# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 234 ሚያዝያ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ጉዞ

**ሞገስ ጸጋዬ**

**ዜና ትንታኔ**

ባለፉት ስድስት ዓመታት በፖለቲካ ዲፕሎማሲ መስክ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ከየትኛውም ጊዜ በላይ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡ ግንኙነቶችን በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥር 2016 ዓ.ም የታተመው «ዲፕሎማሲያችን» ጆርናል እንደሚያመለክተው፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ጉዞ ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት የለውጥ ዓመታት ውጤት ካስመዘገበችባቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች ውስጥ የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲም አንዱ ነው። በሁለትዮሽ ግንኙነት ረገድ ከበርካታ ሀገራት ጋር ግንኙነቷን ማጠናከር ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











ወይዘሮ ሲዲያ ገርማ

## የመዲናዋን ሰላም

### ለማጽናት ሕዝቡ እያደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋን ሰላምና ጸጥታ ለማጽናት ሕዝቡ እያደረገ ያለውን ያላሰለሰ ጥረት አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የመዲናዋን ሰላም ... ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ከውጪ የሚገባውን የእንስሳት መድኃኒት በሀገር ውስጥ ለመተካት ለአምራቾች ድጋፍ እየተደረገ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ከውጭ የሚገባውን የእንስሳት መድኃኒት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ለአምራች ድርጅቶች ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት ሪጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ሰለሞን ከበደ (ዶ/ር) ለኢትየጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከውጭ የሚገባውን የእንስሳት መድኃኒት በሀገር ውስጥ ለመተካት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለአምራች ድርጅቶች ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡

ባለስልጣኑ በውጭ ሀገር መድኃኒት ለሚያመርቱ አካላት የምልከታ ክፍያ ከአራት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ዶላር እንደሚያስከፍል ጠቁመው፤ ለሀገር ውስጥ አምራቾች ይህን ክፍያ እንደማይቀበልም አስረድተዋል፡፡

የግል ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲሰማሩ መንግሥት

ከውጭ የሚገባውን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የምሥራቅ ሸዋ ዞን በመኸር እርሻ 528 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን አቅዷል

## - በክረምት ከ250 ሚሊዮን በላይ የአረንጓዴ አሻራ ችግኞች ይተከላሉ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ዞኑ በመጪው የመኸር እርሻ ወቅት 528 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ማቀዱን የምሥራቅ ሸዋ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በዘንድሮው ክረምትም ከ250 ሚሊዮን በላይ በአረንጓዴ አሻራ ችግኞች እንደሚተከሉም ተገልጿል፡፡

የዞኑ የግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስፍን ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለመጪው የመኸር እርሻ ከጥር ጀምሮ ለአርሶ አደሮች፣ ለባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት እንዲሁም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ዝግጅት ተጀምሯል፡፡

በዚህም በዘንድሮ የመኸር እርሻ ዞኑ 528 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት ማቀዱን ገልጸው፤ ከዚህም 20 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

የመሬት ዝግጅት የመጀመሪያ ዙር እርሻ መታረሱን የገለጹት ኃላፊው፤ እስካሁንም 200 ሺህ ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል ብለዋል፡፡

ከሚለማው መሬት 50 በመቶ የሚሆነው ስንዴ ሲሆን፤ የተቀሩት በሌላ ሰብሎች የሚሸፈን ይሆናል ያሉት አቶ መስፍን፤ በዞኑ የበቆሎ ዘር ቀድሞ የሚዘራ በመሆኑ የዝግጅት ሥራው ተጀምሯል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የዘንድሮ መኸር እርሻ ለየት የሚያደርገው የሜካናይዜሽን ሥራዎችን አጠናክሮ ለመሥራት መታቀዱ መሆኑን የገለጹት አቶ መስፍን፤ አምና 81 በመቶ የነበረውን የቴክኖሎጂ ሽፋን ዘንድሮ 90 በመቶ ለማድረስ ይሠራል ብለዋል፡፡

ኃላፊው፤ ዞኑ አምና የማዳበሪያ አቅርቦት ችግር ሆኖበት መቆየቱን አውስተው፤ ዘንድሮ ድጋሚ ችግሩ እንዳይከሰት ከጥቅምት ጀምሮ ማዳበሪውን የማስገባት ሥራ ቅድሚያ ተሰጥቶት መሠራቱን ጠቁመዋል፡፡

የመጣውን ማዳበሪያ ወደ አርሶ አደሩ የማሰራጨት ሥራዎች እየተከናወ ነው ያሉት አቶ መስፍን ፤ለማግኘት ከታቀደው ማዳበሪያ 90 በመቶ የሚሆነው ወደ ዞኑ መግባቱን ተናግረዋል፡፡

እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለጻ፤ በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩ በዞኑ 279 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዷል፡፡ በሁለት ሺህ 800 የችግኝ ጣቢዎች ችግኞችን ዝግጁ የማድረግ ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡

ከሚተከሉት ችግኞች ውስጥ 40 በመቶ የሚሆኑት ለደን ልማት የሚያገለግሉ ሲሆኑ፤ የተቀሩት ሁለት ጥቅም በሚሰጡ ችግኞች ፣ ፍራፍሬና አትክልት እንዲሁም ለተፋሰስ ልማት በሚያገለግሉ ችግኞች የሚሸፈን መሆኑን ተናግረዋል፡፡

# በግጭቶች ምክንያት የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እየተጓተቱ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር
MINISTRY OF IRRIGATION AND LOWLANDS

አዲስ አበባ፡- በግጭትና የተለያዩ ምክንያቶች የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እየተጓተቱ መሆኑን የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሚዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙነህ ቶልቻ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ አንዳንድ አከባቢዎች እየተከሰተ ያለው ግጭት የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታም ሆነ የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች እንዲስተጓጎሉ ምክንያት ሆኗል፡፡

በግጭት ምክንያት የሰባት መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ እንደተቋረጠ የገለጹት አቶ ብዙነህ፤ አፈጻጸሙ ከ92 በመቶ የተሻገረው የዛሪማ ሜይዴይ የግድብ ግንባታ ከቆሙ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ገለጻ፤ በምዕራብ ሸዋ የሚገኘው የላይኛው ጉደር ሎት አንድና ሁለት፣ የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት አንድና ሁለት፣ አንገር መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት አንድና ሁለት፣ የአባት በለስ፣ የጣና በለስና የላይኛው ርብ ፕሮጀክቶች ግንባታ በግጭት ምክንያት ቆሟል፡፡

ከግንባታው በተጨማሪ ከፍተኛ አፈጻጸም የነበራቸውና መጠናቀቅ የሚችሉ የመስኖ ልማት የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች መቋረጣቸውን አንስተው፤ ከእነኝህም መካከል የአባት በለስ፣ ሎኮአባያ፣ ሞርሞራና ሌሎችም እንደሚገኙበት ጠቁመዋል፡፡

የግንባታ ተቋራጮች አቅም ማነስ ሌላኛው ችግር በመሆኑ ከተቋራጮቹ ጋር በመወያየትና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ በመስጠት ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑንና መሻሻል በማይታይባቸው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

ለአብነትም ለውጥ ባለመታየቱ በስልጤ ዞን የሚገኘው የካሊድ-ዲጆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች ጋር የተደረገው ውል መቋረጡ ተጠቃሽ ነው ብለዋል፡፡

በሲሚንቶና በተለያዩ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ላይ የሚስተዋለውን እጥረትና የዋጋ ንረት ለመፍታት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመሆን በግንባታ ላይ የሚገኙ የሥራ ተቋራጮች ቅድሚያ እንዲያገኙ በተደረገው ጥረት መሻሻሎች ቢታዩም በቂ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

አርሶ አደሮች መሬታቸውን ለመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ቢለቁም ካሳ ባለመከፈሉ ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ በሥራው ላይ ጫና እየደረሰ መሆኑንና ለአብነትም የአጫጫና የወይቦ አካባቢ ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ለአርሶ አደሮቹ የካሳ ክፍያ እንዲያገኙ የማድረጉ ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩል ጎርፍ ለሥራው ትልቁ ተግዳሮት እየሆነ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ብዙነህ፤ በሱማሌ ክልል በምዕራብ ጎዴና ቡልዳሆ አካባቢዎች ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ጎርፉ ለረጅም ጊዜ ተኝቶ የሚቆይ በመሆኑ ማሽነሪዎችን ለማንቀሳቀስ እንቅፋት ሆኗል ነው ያሉት፡፡

መንግሥት የጸጥታ ችግሩን በመፍታት አካባቢውን ለልማት ዝግጁ የማድረግ ሥራ እያከናወነ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በየወቅቱ የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን በመሥራት የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት የራሱን ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ አመልክተዋል፡፡

# አካዳሚው ለአፍሪካ ሀገራት ከፍተኛ አመራሮች ስልጠና እየሰጠ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ለተወጣጡ ከፍተኛ አመራሮች የአመራር ልማት ፕሮግራም ስልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ አስታወቀ፡፡

አካዳሚው ከትናንት በስቲያ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ካደረጉ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት አምባሳደሮች እና ተወካዮች ጋር ውይይት አካሂዷል።

በውይይቱ ወቅት የአካዳሚው ርዕሰ አካዳሚ አቶ ዛዲግ አብረሃ እንደገለጹት፤ አካዳሚው በኢትዮጵያ የአመራር ልህቀት እንዲመጣ ከሚሰራው ሥራ በተጨማሪ የያዘውን ተልዕኮ ለማሳካት ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ለተወጣጡ ከፍተኛ አመራሮች የአመራር ልማት ፕሮግራም ስልጠና እየሰጠ ይገኛል።

የአፍሪካ ለውጥ አራማጅ አመራሮችን በማብቃት የአፍሪካ ውህደት እንዲሳካ ተመሳሳይ የእሳቤ ደረጃ ላይ የሚገኙ አመራሮች እንዲፈጠሩ አካዳሚው እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ብዛት ያላቸውን አፍሪካዊ አመራሮች ማሰልጠንና ማብቃት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንቶች ውስጥ አንዱ ከሌላ የአፍሪካ ሀገር እንዲሆን መፈቀዱንና አፍሪካዊያን በጋራ ሊሰሩ የሚገባበት ጊዜ አሁን መሆኑን የገለጹት አቶ ዛዲግ፤ በጋራ በመሥራት እርስ በእርስ የሚተሳሰሩበትን መንገድ መፈለግ እንዳለባቸውና አካዳሚው ለዚህም ሁነኛ ማስፈፀሚያ መንገድ መሆኑን ተናግረዋል።

አካዳሚው አፍሪካዊ ተቋም እንዲሆን ተድርጎ በመገንባቱ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የምርምር ተቋማት ጋር ያለውን ትብብር ለማሳደግ እየሠራ እንደሚገኝም ጠቁመው፣ አፍሪካዊያን የሚጋሯቸው በርካታ ተመሳሳይ ነገሮች በመኖራቸው ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ ለማፈላለግ አካዳሚውን መጠቀም እንደሚችሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ዛዲግ ገለጻ፤ ቀድሞም ኢትዮጵያ ጆሞ ኬንያታን፣ ኒልሰን ማንዴላንና ሌሎችንም የአፍሪካ መሪዎች አሰልጥናለች፡፡ አሁን በተሻለ ቁመና ላይ የምትገኝ በመሆኑ የአሁኑ ትውልድ ለራሱ ችግር ብቻ ግድ የሚሰጠው ሳይሆን የአፍሪካ ችግርም እንዲቃለሉ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችል ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

ከ11 የአፍሪካ ሀገራት ተቋማት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስምምነት መደረጉንና ይህንንም የማስፋት ሥራ እንደሚከናወን ያነሱት አቶ ዛዲግ፤ አካዳሚው በትንሹ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ብቻ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ለተወጣጡ 120 ከፍተኛ አመራሮች ስልጠና መስጠቱን ገልጸዋል።

ተሳታፊዎች በበኩላቸው አካዳሚው ይዞት የተነሳው እጅግ የሚደነቅ ሃሳብ በመሆኑ እንደሚደግፉት በመግለፅ፤ የተያዘው ውጥን ከግብ እንዲደርስ ከመሰል አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በጋራ መሥራት እንዳለበት አመላክተዋል።



አቶ ዛዲግ አብረሃ

# የሱዳን ጦርነት በአፍሪካ ቀንድ ያስከተለው ተጽዕኖና መፍትሔ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

በሱዳን እየተካሄደ ያለው ጦርነት ኢትዮጵያን ጨምሮ በቀጣናው በሚገኙ ሀገራት ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ተመራማሪ በፍቃዱ ቦጋለ (ፐ/ር) እንደሚሉት፤ ይህ ጦርነት ለአፍሪካ ሀገራት በተለይም ለቀጣናው ሀገራት ያለው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡

ፕሮፌሰር በፍቃዱ እንደሚሉት፤ ከሱዳን የእርስ በእርስ ጦርነት ጀርባ የተለያዩ ሀገራትና ተቋማት ድብቅ አጀንዳ አለ፤ በመሆኑም ጦርነቱን በቀላሉ ለመቋጨት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ ያም ሆኖ ግን በተለይ ኢትዮጵያ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ያደረገችው ጥረት አበረታች ነው፡፡

ሁለቱን ኃይሎች በተለያዩ ሀገራት ለማሸማገል ጥረት ሲደረግ ቆይቷል ያሉት ፕሮፌሰር በፍቃዱ ፤ ኢጋድ፣ አፍሪካ ኅብረትና ደቡብ ሱዳን በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ጥረት ካደረጉት መካከል ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል፡፡

በዩክሬንና በራሽያ ጦርነት፣ በጋዛ ጦርነት ምክንያት ለሱዳኑ ጦርነት ትኩረት መነፈጉ እንዲሁም አረብና ጥቁር አፍሪካዊያን ነን የሚል የሱዳን ዜጎች የሃሳብ ክፍፍል ጦርነቱን የማይጨበጥ ማድረጉም ተጨማሪ ምክንያቶች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ በሀገሪቷ የተፈጠረው



በፍቃዱ ቦጋለ(ፐ/ር)



አደም ካሚል(ረ/ፐ/ር)

አለመረጋጋት ከሰላም መደፍረስና ቀጣናዊ ትብብርን ከማቀጨጭ አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በተለይ ሱዳን ከሕገ-ወጥ የሰዎችና የጦር መሳሪያ ዝውውር አንጻር መሸጋገሪያ በመሆኗ በቀጣናው ላይ ከፍተኛ ችግር ማስከተሉን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም በቀጣናው ያሉ ተቋማት እንዲዳከሙ፣ የተጠናከረ ትብብር እንዳይኖር እንዲሁም ሽብርተኝነት በጋራ መዋጋት እንዳይቻል ማድረጉንም ነው ፕሮፌሰር በፍቃዱ ያመላከቱት፡፡

ጦርነቱ ከኢትዮጵያ ጥቅም አንጻር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ቢኖረውም በኢትዮጵያ በኩል ባለው ከፍተኛ ጥንቃቄ እስካሁን ከሌሎች የተለየ ተጽዕኖ ያሳደረባት ነገር አለመኖሩን ተናግረዋል፡፡

መሰል ጦርነቶች በቀታናው ሀገራት እንዳይከሰቱ ሀገራዊ የተቋማት ግንባታ ማጎልበት፣ የልዩነት ምንጮችና አድሎአዊ አሰራሮች ከመሰረታቸው በፊት ማድረቅ እንዲሁም የውጭ ጣልቃ ገብነት ማስወገድ አስፈላጊ ነውም ብለዋል፡፡

በተለይ ጦርነቱ የሚቀጥል ከሆነ ሱዳን ከደቡብ ሱዳን ጋር በድንበር ውዝግብና ከነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ጋር ተያይዞ ያልተቋጩ ጉዳዮች በመኖራቸው ለቀጣናው ሌላ ራስ ምታት እንዳይሆን የሚል ስጋት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

የሱዳኑ ጦርነት ወደ ሰላም እንዲመጣ ኢትዮጵያ ከአረብ ሊግና ከሌሎች ሀገራትና ተቋማት በላይ ጥረት አድርጋለች ያሉት ደግሞ ኢት-አረብ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የጥናትና የምርምር ባለሙያ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ናቸው፡፡

ጦርነቱ ለአፍሪካ ሀገራት ለከባድ ችግር እየዳረገ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ኢትዮጵያ ባላት በሳል ዲፕሎማቲክ አካሄድ ከፍተኛ ተጽዕኖ መፍጠር ትችላለች ብለዋል፡፡

እንደ ረ/ፕሮፌሰር አደም ገለጻ፤ የአፍሪካ ኅብረት፣ የአረብ ሊግ፣ ኢጋድ እንዲሁም የቀጣናው ሀገራት ያደረጉት ርብርብ ፍሬ እንዳያፈራ ያደረገው የሌሎች ሀገራት ድብቅ አጀንዳ እንዲሁም ሀይ ባይ ያጣው የመሳሪያ ንግድ ነው፡፡

በሀገሪቱ የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ለመገንባት ከመቶ ዓመት በላይ ይወስዳል ያሉት ረ/ፕሮፌሰር አደም፤ አሁንም ከዚህ በላይ ጉዳት እንዳያስከትል ሁሉም ተረባርቦ ተዋጊ ኃይሎች ከስምምነት እንዲደርሱ የበኩሉን መወጣት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ምሁራኑ እንደሚሉት፤ የሱዳን ጦርነት በጊዜ ካልተቋጨ በአፍሪካ ቀንድ ብሎም በአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በሀገሪቱ ሰላም የሚሰፍንበትን ሁኔታ መፍጠር ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡

# ፕሮጀክቱ ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን

## በላይ ስደተኞችንና የስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ ያደርጋል

- **በፕሮጀክቶቹ የተገዙ 77 የመስክ መኪናዎች ለፌዴራል ተቋማትና ለክልሎች ተሰጥቷል**

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚተገበረው የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት ምዕራፍ ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ስደተኞችንና የስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተገለጸ።

የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት እና በአደጋ ስጋት ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት በጋራ በመሆን 289 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ 77 ተሽከርካሪዎችን ለክልሎችና ለፌዴራል ተቋማት ርክክብ አድርገዋል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ(ዶ/ር ) በወቅቱ በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚተገበረው የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት 54 ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም የአደጋ ስጋት ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት 23 ተሽከርካሪዎችንና አንድ ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ክሊኒክ 289 ሚሊዮን ብር በሚገመት ወጪ ለክልሎችና ለፌዴራል ተቋማት ማበርከታቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የስደተኛ ተመላሽ ፕሮጀክት 265 ሞተር ብስክሌቶች ገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ መሆኑን ገልጸዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የስደተኞች ተፅዕኖ ምላሽ የልማት ፕሮጀክት ምዕራፍ ሁለት ብሄራዊ አስተባባሪ አቶ ንጋቱ ቦጋለ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ በስድስት ክልሎች፣ በ30ወረዳዎች፣ በ330 ቀበሌዎች እና በ25 የስደተኛ መጠለያዎች ላይ እየተተገበረ ይገኛል።

በዚህም ከአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ




ስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰብንና ከ750ሺ በላይ ስደተኞችን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

አቶ ንጋቱ ፕሮጀክቱ ለአምስት ዓመታት በ180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚተገበር ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ፕሮጀክቱ ለሚከናወንባቸው ክልሎች 145 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ የተገዙ 54 ተሽከርካሪዎችን ማበርከቱን ገልጸዋል።

አቶ ንጋቱ ፕሮጀክቱ በምእራፍ አንድ ትግበራው ስደተኞችን ባስጠለሉ 5 ክልሎችና 16 ወረዳዎች ላይ በዓለም ባንክ በተገኘ 100 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ድጋፍ የስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰቦችን እና ስደተኞችን ተጠቃሚ ያደረጉ የልማት ሥራዎችም መከናወናቸውን አብራርተዋል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የአደጋ ስጋት ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት ብሄራዊ አስተባባሪ አቶ ጀማል አልዬ በበኩላቸው፤ ለኦሮሚያ፣ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ለደቡብ ኢትዮጵያ፣ ለሶማሊያ እና ለአፋር ክልሎች እንዲሁም ሥራውን ለሚያስተባብሩ ለግብርና ሚኒስቴር፣ ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሚሰራጩ 23 የተለያዩ ዓይነት ቶዮታ ሃርድ ቶፕ እና አንድ ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና መስጫ ክሊኒክ ግዥ መፈፀሙን ተናግረዋል።

# የኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ በአፍሪካ አንድነትና ኅብረት ምስረታና የሥራ እንቅስቃሴ የተመዘገበው የዲፕሎማሲ ድል ቀጣይነት ለማረጋገጥ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ ብሪክስን በመቀላቀል ያገኘችው ድል ተጠቃሽ ነው። ድሉ በቀላሉ የተመዘገበ ሳይሆን በሳልና ውጤታማ የዲፕሎማሲ ትግል ተደርጎበት የተገኘ ነው ሲል ሰነዱ ያብራራል።

ኢትዮጵያ ይህን ተቋም የተቀላቀለችው ከአንድ ጎራ ወጥታ ወደ ሌላ ለመቀላቀል ሳይሆን መነሻውም መድረሻውም ብሄራዊ ጥቅም የማረጋገጥ ጉዳይ መሆኑን ጀርናሉ ያስረዳል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ በአፍሪካ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃና በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ግንኙነት ያጠቃልላል የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል፤ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ከጥንት ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ችግር አለበት፡፡ በተለይ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር በታሪክ፣ በቋንቋ፣ በእምነት፣ በቅርበት፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና የንግድ ግንኙነት ቢኖርም ግንኙነቱ በሚፈለገው ልክ ሳያድግ ቆይቷል፡፡ይህም ኢትዮጵያም በርካታ ጫናዎች እንዲደርሱባት ምክንያት ሆኗታል ይላሉ፡፡

የዓባይ ውሃ ጉዳይ ለኢትዮጵያና ለመካከለኛው ምሥራቅ ግንኙነት የትስስር ምንጭ ነው ያሉት አደም፤ ክርስትና፣ እስልምናና አይሁድ ከመካከለኛው ምሥራቅ የመጡ እምነቶች ናቸው፡፡ ይህም ትልቅ ትስስር ፈጥሯል፡፡

ከስድስት ዓመት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ስልጣን ሲመጡ እየተንከባለለ የመጣውንና ያልተጠቀምንበትን የመካከለኛው ምሥራቅ ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረግ ተችሏል፡፡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲው ስለመጠናከሩ በመግለጽ፤ ውጤትም ተገኝቶበታል ነው ያሉት፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት የተጀመረውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል አረብኛ ቋንቋ የሚችሉ ዲፕሎማቶችን መመደብ አስፈላጊ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት የተመዘገቡ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ውጤቶችን ማዳበር ያስፈልጋል፡ ፡ የቱሪዝምና የንግድ ልውውጡ እያደገ መጥቷል፡፡

እንዲሁም ባለፉት ስድስት ዓመታት ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እያበረከተች ያለው አስተዋጽኦ ቀላል አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ይበልጥ ተሰሚነቷን በማሳደግ የዲፕሎማሲ ጉዞዋን ውጤታማ ለማድረግ ከዲፕሎማት አመዳደብ ጀምሮ ያሏትን ጠንካራ ጎኖች መጠቀም አለባት፡፡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋን መፈተሽና የውስጥ ሰላም ማስፈን ይገባል ይላሉ፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት የዲፕሎማሲ ጉዞ ለኢትዮጵያ አልጋ በአልጋ ነው ማለት ባይቻልም በፖለቲካ ዲፕሎማሲው መስክ ተጨባጭ ውጤቶች የተገኙበት ነው፡፡ ከጎረቤት ሀገራት ጀምሮ ቀደም ሲል እምብዛም ጠንካራ ግንኙነት ካልነበራት የላቲን አሜሪካ፣ የካሪቢያን ሀገራት፣ሩቅ ምሥራቅና መካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር ጠንካራ የሁለትዮሽ ግንኙነት መፍጠር ተችሏል፡፡ ሚሲዮን በአዲስ አበባ የከፈቱ ሀገራት ቁጥርም እየጨመረ ሲሆን አንድ መቶ 34 መድረሱንም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መስራችና አባል ብትሆንም ባለፉት ስድስት ዓመታትም ይህን ታሪኳን በማስቀጠል የብሪክስ ጥምረት ሀገራት አባል ሆናለች፡፡ ይህም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ውጤትን ያሳያል፡፡ በተለያዩ ሀገራት በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱና በሚኖሩበት ሀገር ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ የተሰራው የዲፕሎማሲ ሥራ ባለፉት ስድስት ዓመታት ከተገኙት የዲፕሎማሲ ውጤቶች መካከል የሚጠቀስ መሆኑን ምሁሩ ይገልጻሉ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ነብዩ ተድላ በበኩላቸው፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት የተመዘገቡ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ስኬቶችን አስመልክቶ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ አዲስ የዲፕሎማሲ ጉዞ ውጤት የተገኘበት ነው፡፡ በተለይ በፖለቲካ ዲፕሎማሲ መስክ ከሀገራት ጋር ጥሩ የሁለትዮሽ ግንኙነት መፍጠር ተችሏል። በርካታ ሀገራት ኤምባሲያቸውን በአዲስ አበባ የከፈቱበትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የተጠበቀበት ነው፡፡

ባለፉት ሦስት ዓመታት ያጋጠሙ ችግሮችንና የውጭ ጫናዎችን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መፍታት መቻሉንም ያስረዳሉ፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ስልጣን ከመጡ ማግስት ጀምሮ መሥራታቸውን የገለጹት አቶ ነብዩ፤ በዚህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር ተችሏል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር አይተኬ ሚና ተጫውታለች፡፡ ኢትዮጵያ ለሰላም የሠራችው ሥራ ዓለም እውቅና የሰጠው ነው፤ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኖቤል የሰላም ሽልማት ያሰጠ መሆኑን አውስተዋል፡፡ አሁንም ኢትዮጵያ ባለችበት ቀጣና ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ጠንካራ ሚናዋን በመወጣት ላይ ትገኛለች ይላሉ፡፡

የቀጣናው የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጎለብት በፖለቲካ ዲፕሎማሲው ረገድ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ይህም ኢትዮጵያን የቀጣናው የስህበት ማዕከል ሆና እንድትቀጥል አድርጓታል፡፡ በለውጡ ዓመታት ውስጥ ትልቅ ዲፕሎማሲ ድል ተደርጎ የሚቆጠረው የብሪክስ ጥምረት አባል መሆኗ ነው። ይህ ጥምረት ለኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ቅቡልነቷን እንደሚያሰፋ አቶ ነብዩ በማሳያነት ጠቅሰዋል፡፡

# ከውጭ የሚገባውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በለሚ ፓርክ የመሥሪያ ቦታዎችን ማመቻቸቱን ጠቁመው፤ የእንስሳት ክትባት ከዶሮ ውጪ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ በሚገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራቾች የሚሸፈን ሲሆን 95 በመቶ የሚሆነው የእንስሳት መድኃኒት አሁንም ከውጭ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ለሀገር ውስጥ አምራቾች ምርታቸውን በሚፈለገው ልክ እንዳያመርቱ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት እንቅፋት እንደሆነባቸው መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል፡፡

በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር የሚገባውን መድኃኒት ለማወቅ እንደ ሀገር ጥናት መደረጉን ጠቅሰው፤ ከጸጥታ ጋር በተገናኘ በድንበር አካባቢ የተወሰነ የመድኃኒት ዝውውር መኖሩን ማወቅ ተችሏል ብለዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የሚሸፈነውን አምስት በመቶ የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦት ለማሻሻል በዘርፉ ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ አምራቾች ድጋፍ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሰለሞን (ዶ/ር) ገለጻ፤ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪዎች ከአምራቹ በተሻለ ትርፋማ መሆናቸው አምራቾች ወደ ዘርፉ እንዳይቀላቀሉ አድርጓቸዋል፡፡

ለአምራቾች ቅድሚያ ያለመስጠት ሁኔታዎች መኖራቸው አምራቾች ውጤታማ እንዳይሆኑ እንዳደረገ ገልጸው፤ የክልል ግብርና ቢሮዎች የመድኃኒት ግዢ በሚፈጽሙ ጊዜ ለሀገር ውስጥ አምራቾች ቅድሚያ በመስጠት መደገፍ ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ አምራቾች እንዲበረታቱ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

አሁን ላይ አዳሚ ቱሉና ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ከክትባት ባለፈ የእንስሳት መድኃኒት እያመረቱ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ኢስት አፍሪካ የመድኃኒት ፋብሪካ ወደ ማምረት እንደሚመለስ ጠቁመዋል፡፡

ባለስልጣኑ ቃሊቲ በሚገኘው መመርመሪያ ማዕከል ከውጭ የሚገቡና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ መድኃኒቶችን በመፈተሽ ወደ ገበያ እንዲገቡ እንደሚያደርግ አመላክተዋል፡፡



# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕገወጥ ግንባታን በተገቢው መንገድ እንከላከል!

እንደ ሀገር ሕግ እና ሕጋዊነትን ለማስፈን በመንግሥት ደረጃ ከፍተኛ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በዚህም እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶች ተስፋ ሰጪ ቢሆኑም፣ በተለያዩ መንገዶች እና ሁኔዎች የሚፈጠሩ ሕገ ወጥነቶች ግን አሁንም ሀገር እና ሕዝብን ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ ናቸው።

በተለይም በከተሞች አካባቢ ከሚካሄዱ ከግንባታ ጋር በተያያዘ እየተስተዋሉ ያሉ ሕገወጥነቶች ፣በሀገር ሀብት ላይ እያስከተሉት ያለው ጥፋት ከፍተኛ ነው ።በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ባለው ግንኙነት ላይም እየፈጠሩ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖም በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በየትኛውም ዓለም መንግሥት ሕግ እና ሥርዓትን የማስጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፤ ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ ሕጎችን በማርቀቅ በሚመለከታቸው አካላት አጸድቆ ወደ ሥራ የሚገቡበትን አግባብ ያመቻቻል ።ለሕጎቹ ተፈጻሚነትን ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ ባለው አቅም ይሠራል።

በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚደረጉ የግንባታ ሥራዎች ፣ አጠቃላይ የሆነውን ቀጣይ ሀገራዊ የከተሞች ልማት ታሳቢ ባደረገ መንገድ በፕላን የሚመሩበትን የሕግ እና የአሠራር ሥርዓት ያስቀምጣል፣በተጨባጭ ተግባራዊ መሆናቸውንም በጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ይከታተላል።

የከተሞች ልማት በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚከናወን ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ፣ ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገዎችንም ታሳቢ የሚያደርግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የሚያካትት ነው። በተለይም እንደኛ ባሉ ከተሞችን በሚፈልጉበት መንገድ ለመገንባት የሀብት ውስንነት ያላቸው ሀገራት ያላቸውን ውስን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የከተሞች ልማትን በከፍተኛ ጥንቃቄ ለመምራት ይገደዳሉ ።

በተለይም ዜጎች ባላቸው አቅም በከተሞች ልማት ውስጥ የሚሳተፉበትን ፤ለከተሞች እድገት አቅም ሆነው የሚያገለግሉበትን እድል በመፍጠር ሂደት ውስጥ የመንግሥት ኃላፊነት ከፍተኛ ነው። ይህ ኃላፊነቱ የከተሞችን ልማት ግልጽ በሆነ ፖሊሲ ከመምራት ጀምሮ፤ዜጎች የከተሞች ልማት ስትራቴጂክ አቅም የሚሆኑበትን አስቻይ ሁኔታ መፍጠርን ያካትታል።

በሀገራችን ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ ብዛት ያላቸው ከተሞች ቢኖሩም ፤ለከተሞች ልማት ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠቱ የእድሜያቸውን ያህል ዘመናዊነት ተላብሰው ለነዋሪዎቻቸው የተሻሉ የመኖሪያ ስፍራ መሆን የቻሉ አይደሉም። ይህ እውነታ በአፍሪካ መዲናነቷ በምትታወቀው የሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባም በግልፅ የሚስተዋል ነው።

አዲስ አበባ ከመቶ ዓመት የበለጠ የእድሜ ባለጸጋ ብትሆንም ፤ከተቆረቆረችበት ጊዜ አንስቶ በተከሰቱ እና ዛሬም ድረስ በሚከሰቱ፤ እድገቷን በሚፈታተኑ ችግሮች ስትጠላለፍ ቆይታለች።

ከነዚህም ውስጥ በዋንኛነት የሚጠቀሰው የሕገ ወጥ ግንባታ ነው ። ባልተገባ መንገድ የከተማዋን ፕላን እና ነገዎች በሚፈታተን መንገድ የሚከናወኑ እነዚህ ሕገወጥ ግንባታዎች ፤ የከተማዋን ገጽታ ከማበላሸት በተጨማሪ የከተማ ውስጥ መሠረተ ልማት ግንባታዎችን በቀላሉ ለማከናወን የሚደረጉ ጥረቶችን በፈተና የተሞሉ አድርጓቸዋል።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመቅረፍ በሚል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማ ደረጃ የደንብ ማስከበር ቢሮ ቢደራጅም፤ ቢሮው በራሱ በተለያዩ ሕገወጥ አሠራሮች ተጠላልፎ ለችግሩ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ያለ ከልካይ በጠራራ ፀሐይ ብዙ ሀብት ፈሶባቸው የተገነቡ ሕገወጥ ግንባታዎች ፤በጠራራ ፀሐይ ሕገወጥ ተብለው የሚፈርሱበት ሁኔታ የብዙዎችን ልብ የሰበረ፤ እንደ ሀገር የፖለቲካ አጀንዳ ሆኖ፤ ሀገርን ላልተገባ ብዙ ጥፋት የዳረገ ነው።

ሰፊ ሀብትና የሰው ኃይል እየተሳተፈበት ባለው ሕገወጥ ግንባታን የመቆጣጠር የመንግሥት ጥረት፤ በራሱ በተቆጣጣሪው ተቋም ውስጥ ባለ የተበላሸ አሠራር የተጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልቻለም። እንዲያውም ለውጡን ለሚጻረሩ ኃይሎች የፖለቲካ አጀንዳ በመሆን በለውጡ መንፈስ ላይ ያልተገባ ጥላ እንዲያጠላ አድርጓል።

ችግሩን ዛሬም ሙሉ በሙሉ የተፈታ/የተሻገርነው አይደለም ።አሁንም በየጥጋጥጉ እና በየመንደሩ ሕገወጥ ግንባታ በእጅ መንሻ እየተካሄዱ ነው። ለዚህ ደግሞ ጠዋት ፈርሰው ማታ ላይ ተመልሰው የሚገነቡ ሕገወጥ ግንባታዎችን መመልከት በቂ ነው።

ለዘለቄታው ችግር ለመፍታት ከሁሉም በፊት፤ ደንብ አስከባሪ በስፋት ከማሰማራት እና ችግሩን ለመከላከል ከመሞከር በፊት ግልጽ እና ቀልጣፋ የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ ማውጣት እና በመመሪያው ዙሪያ ሕዝቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማስቻል ያስፈልጋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ለተሰጠው ኃላፊነት ታማኝ የሆነ ባለሙያ ማፍራት ፤ተጠያቂነትን ማስፈን የሚያስችል ጠንካራ አሠራር ማስፈን ያስፈልጋል ።ከዚህ ውጪ በራሱ ሕገወጥ የሆነ ኃይል አሰልፎ ሕገ ወጥነትን መከላከል አይቻልም። በዚህ መልኩ ሕገወጥነትን ለመከላከል የሚደረግ ጥረት እንደቀደመው ጊዜ የሕዝብን ሀብት ለጥፋት ከመዳረግ፤ በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት ከማበላሸት ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስደትን የሚያሳድዱ

ስምስም መንግሥቱ

የጅልባ መገልበጥ ደርሶ ባህር ውስጥ ይሄን ያህል ሰዎች ሰመጡ፣ በበረሃ ሲጓዙ ይሄን ያህል ሰዎች ተጎዱ፣ ከፎቅ ተወርውረው ሞቱ፣ የአካል ጉዳተኛ ሆኑ፣ ተደፈሩ፣ የሥነልቦና ጥቃት ደረሰባቸው፣ ሰብአዊ መብታቸው ተጣሱ የሚሉ ወሬዎችን መስማት ከጀመርን ዓመታት ተቆጥረዋል።

ይባስ ብሎ ደግሞ በኑሮ ለመለወጥ ነገን ተስፋ አድርገው፣ በደላላ ተዋክበው፣ ነፍሳቸውን አስይዘው፣ ጥሪታቸውን አሟጠው፣ ያሰቡት ቦታ ደርሰው እቅዳቸውን ለማሳካት ደፋ ቀና እያሉ በሀገሬው የፀጥታ ኃይል ታፍሰው እስር ቤት የሚታጎሩትም ብዙ ናቸው።

ለቤተሰቤ መከታ እሆናለሁ፤እኔም ያልፍልኛል ብለው ከሀገር የወጡ ወጣቶች ያሰቡት እንዳይሆን ሆኑ ለበርካታ ውጣ ውረዶች ይዳረጋሉ።በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከመኖር ብዙዎች ወደ ሀገር ቤት መመለስን ቢፈልጉም ወላጆች ያላቸውን ጥሪት አሟጠው የሰጧቸውን ገንዘብ፣ ከፊሎቹም ዘመድ ወዳጅ አስቸግረው ተበድረው የወሰዱትን ገንዘብ ሳይመልሱ፣ እራሳቸውን ለውጠው የቤተሰባቸውንም ኑሮ ለማሻሻል አቅደው ከትምህርት ገበታቸውም ተስተጓጉለው፤ ቤተሰብም ተስፋ አድርጎባቸው፣ ጎረቤቱም መርቆ ሸኝቷቸው እቅዳቸውን ከዳር ሳያደርሱ ባዶ እጃቸውን መመለሳቸው ውስጣቸውን ያርደዋል።

እስር ቤት ገብተው አስታዋሽ አጥተው ለዓመታት በእስር ቤት ውስጥ የሚቆዩ፣ ለጤና ችግር ተዳርገው የሚሰቃዩ እና አለፍ ሲልም እስር ቤት እያሉ ለሞት የሚዳረጉ ጥቂት አለመሆናቸው በተለያየ ጊዜ የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ።ይህንኑ የተረዳው የኢትዮጵያ መንግሥትም ለእነዚህ ወገኖች አለኝታ በመሆን ላይ ይገኛል።

ትናንት አስታዋሽ ያልነበራቸው ዜጎች ዛሬ መንግሥት ባደረጋቸው ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ከእስር ቤት ወጥተው የሀገራቸውን መሬት ለመሳም በቅተዋል። በህይወት ተርፈው ለሀገራቸው መሬት የበቁትም ዝቅም ብለው አፈሯን ሲስሙ ተመልክተናል።

ከተመላሾች ውስጥም ከሳውድአረቢያ የሚመለሱት ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ ቢሆኑም ከኦማን፣ ከየመን፣ በሱዳን በተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ለረጅም ዓመታት በሱዳን ኑሮአቸውን አድርገው የነበሩ ኢትዮጵያን ሁሉ ሳይቀር ወደ ሀገራቸው በመመለስ ላይ ይገኛሉ።

ስደትን ምርጫው አድርገው ባልተገባ መንገድ ወይንም በሕገወጥ ለመሄድ የሚነሳሱት ዜጎች ለጉዞ በርካታ ገንዘብ ያወጣሉ። በትንሹ እስከ 100ሺ ብር እንደሚያወጡ ተጓዦቹ ይናገራሉ። ታዲያ በዚህ ገንዘብ እንደአቅማቸው ሀገራቸው ላይ መስራት አልፈለጉም የሚል ጥያቄ ያስነሳል።ተጓዦቹ እንደሚናገሩት፤ ለሕገወጥ ስደት የሚዳረጉት ከእነሱ ፍላጎት በላይ ወላጆችም ጭምር ስለሚፈልጉት ነው።

እንደውም በአንዳንድ አካባቢዎች ወላጆች የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ልጆቻቸውን ለሕገወጥ ስደት መርቀው የሚሸኙበት ሁኔታ መኖሩንና ይህም ሁኔታ ሕገ ወጥነትን ትክክል አድርጎ የመቀበልና ተጓዦችንም የሚያበረታታ ሆኖ የመገኘቱ ሁኔታ መንግሥትም ደርሶበታል። ይህም ልጆቻቸውን አሳልፈው ለችግር ለመስጠት ግድ የማይሰጣቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ማፍራት ደረጃ ላይ መደረሱ ነገሩን ከባድ ያደርገዋል።

ከድህነት እና ከቤተሰብ ግፊት ባሻገር በተፈጥሮ አደጋ እንደ ጎርፍ፣ ድርቅ እንዲሁም በተለያየ መንገድ በሚፈጠር ግጭት ሰዎች ቀዬያቸውን ለቀው ወደሌላ አካባቢ ለመሄድ ይገደዳሉ። ሀገር አቋርጠው ለመሄድም ገፊ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ያሉ አስገዳጅ ሁኔታዎች መኖራቸው ቢታወቅም፤ የብዙዎቹ በተለይም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገር የሚሄዱት ዜጎች ኑሮን ከመቀየር ጋር የተያያዘ ነው።

የተሰደደ ሁሉ ያልፍለታል በሚል እሳቤ አብዛኛው ወጣት ትምህርቱን አቋርጦ መሰደድን ህልሙ ያደርጋል።ገና ሁለተኛ ደረጃ ሳይደርስ የሚያልመው ሀገር ለቆ መሰሰድን ነው። ምኞቱን ተስፋውን ይዞ ያለምንም በቂ ዝግጅት ድንበር አቋርጦ፤ኬላ አሰባብሮ መጓዝ እና በረሃን ሰንቆ ካሰቡበት መድረስ ብዙ ወጣቶች የእለት ተዕለት ህልም ነው።

ስለሚሄዱበት ሀገር ባህልና ቋንቋ፣ ስለሚሰሩትና ለሥራው ብቁ ስለመሆናቸው፣ በቂ የሆነ መረጃ ለመያዝ ወደ አእምሮአቸውም አያስገቡም። እንደምንም ገንዘብ አፈላልገው ለመሄድ ነው ፍላጎታቸው። በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አንዲት ሴት ልጅ ስምንተኛ ክፍል ከደረሰች በኋላ ከዚያ በኋላ ትምህርት ለመቀጠል ፍላጎት የላትም ፤ህልሟ ሁሉ አረብ ሀገር መሄድ ነው።

ደላላውም እንዲህ ያለውን ሥነልቦና ነው የሚጠቀመው። ከሰማይ ገንዘብ የሚወርድላቸው እስኪመስላቸው ድረስ ልባቸው በፍላጎት እንዲነሳሳ እንጂ ያለውን ውጣ ውረድ አይነግራቸውም። በተለይ ከገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል የሚሰደዱት የከተማን ህይወት በአግባቡ ሳይረዱ ዘመናዊ ወደ ሆነ ከተማ ለመጓዝ ሲነሳሱ ከማያውቁት ዓለም ጋር መጋጨታቸው አይቀሬ ነው።

አሁን ላይ የጉዞ ሰነድ ሁሉም በአካባቢው ላይ የሚያገኙበት ሁኔታ ምቹ ከመሆኑ በፊት የጉዞ ሰነድ ለመውሰድ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው በአታላዮች ገንዘባቸው የሚወሰድባቸው፤የሚደፈሩና የሚንገላቱ ብዙዎች ነበሩ። ስለዚህም ስቃዩ የሚጀምረው ገና ከሀገር ሳይወጡ ነው ማለት ነው።

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ሄደው ግን ደግሞ ተይዘው ወደሀገራቸው የተመለሱ ዜጎች የማይድን ጠባሳ ይዘው ይቀራሉ። ከነዚህ የስደት ተመላሾች መካከል ለሳምባ፣ ለቆዳና ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ፣ የት እንዳሉና ስለቤተሰባቸው ማወቅ የተሳናቸው የአእምሮ ህመም የገጠማቸው፣ በምን ሁኔታ እንኳን በቀዶ ጥገና ከሰውነታቸው ክፍል አካላቸው እንደተወሰደባቸው በትክክል የማያውቁ፣ የተለያየ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ይገኙባቸዋል።

ምንም አይነት የጉዞ ሰነድ የሌላቸው መኖራቸው ደግሞ በማስመለሱ ሂደት ላይ የሚፈጥረው ጫና ችግሩ ውስብስብ መሆኑን ነው ከመንግሥት መረጃ የሚሰማው። ከስደት ተመላሾቹ ሀገራቸው ሲገቡ መሬት ተደፍተው ሲስሙ የነበሩበት አስቸጋሪ ሁኔታ ምን ያህል ከባድ እንደነበር መረዳት አያዳግትም።

ይሄን ሁሉ ልብ ያለው ልብ ሳይል ስደትን ማሳደዱ ለምን የሚል ጥያቄ በብዙዎች መፈጠሩ አይቀርም። በተለይም ሕገወጥነት ከዓላማ እንደሚያሰናክል እየታየ ካለው ጉዳት በላይ ምን ማስረጃ ማምጣት ይቻላል።

በሕገወጥ ጉዞ ምክንያት እየተፈጠረ ያለው ጉዳት የዜጎችን ሰብአዊ መብት ከመጣስ በተጨማሪ የሀገር ገጽታንም ያጠለሻል። ከስደት ለሚመለሱ ዜጎች የትራንስፖርት አገልግሎት ከመስጠት ጀምሮ በመጠለያ አቆይቶና የተለያዩ ድጋፎችን አድርጎ ወደቤተሰብ መቀላቀልና የሥራ ዕድለም ምቹ ማድረግ ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጫና የሚያሳድር መሆኑም ልብ ሊባል ይገባል።

እንዲህ ያለውን ተደራራቢ ጫና ለማስቀረትም ሆነ ሕጋዊ ያልሆነ ፍልሰትን ለመከላከል ለመንግሥት ብቻ የሚተው እንዳልሆነም ከችግሩ ስፋት መገንዘብ ይቻላል። በሕገወጥ ስደት ውስጥ ያሉት ተዋናዮች ከሀገርም ያለፈ በመሆኑ ሀገራት በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ከጦር መሳሪያና ከአደንዛዥ እጽ ዝውውር ቀጥሎ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አደገኛ በሚባለው ውስጥ የሚፈረጅ በመሆኑ ትብብሩ ሊጠናከር ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞኒ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር”100ኛ ዓመትን የማክበር ምጸት፤

**(ክፍል አንድ)**

ባለፈው ሐሙስ ሚያዚያ 17፣2016 ዓ.ም አንድ ጉምቱ የኢኮኖሚክስ ሊቃ ከአንድ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ጋር ሰምነኛ የመንግሥት ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ማለትም የችርቻሮ፣ የጅምላ፣ የገቢና ወጪ ንግድ ለውጭ ዜጎችና ኩባንያዎች ክፍት መደረጉ ስለሚኖረው አንድምታ ሲያብራሩ ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ(1879-1912 ዓ.ም) ስለገቢና ወጪ ንግድ በምሳሌ ያቀረቡትን ትንታኔ ሲያወሱ በእግረ መንገዳቸው፤”መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” የተሰኘው የነጋድራስ መጽሐፍ የታተመበት 100ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በሳይንስ አካዳሚ ውይይት መካሄዱን ሲናገሩ ጆሮዬ ጥልቅ አለ። የሰማሁት ነገር የተደበላለቀ ስሜት ፈጠረብኝ።

በሀገራችን ኢኮኖሚ፣ በሕዝባችን ኑሮ ተርጉመን ያልገለጥነውን፤ ከመጽሐፍ መደርደሪያ ያላወረድነውን፤ አቧራውን አራግፈን ብናወርደውም ከምርምር ርካታ በላይ ሥራ ላይ ያላዋልነውን፤ በምትኩ የአዳም ስሚዝን ነፃ ገበያ፤ የእነ ኤንግልስን ሶሻሊዝም እንደወረደ ስንኮርጅ ኖረን፤ ፋና ወጊውን የነጋድራስ የፖለቲካል ኢኮኖሚ መጽሐፍ 100ኛ ዓመት ልደት ማክበር ምን ይሉታል። ምጸት እንጂ። አበው እማው የወለፈንዲ ስልቻ ጤፍ ያፈሳል ባቄላ ይቋጥራል እንዳሉት። ነጋድራስ ከመቃብር ቀና ብሎ ቢያንስ ምን ይለን። ምን ይታዘበን። መቼም ሌላው ቢቀር በስጨት ብሎ መጽሐፉን የጻፍሁት እኮ ዓመት እየቆጠራችሁ ልደት እንድታከብሩለት፣ ሻማ እንድታበሩለት ሳይሆን ሥራ ላይ አውላችሁ የሀገርንም የሕዝብን ኑሮ እንድትቀይሩበት ነው ማለቱ አይቀርም። ሲጀመር ይሄን ልደት የማክበርስ የቅስም ወይም የሞራል ልዕልና አለን ወይ የሚለውን ጥያቄ እግረ መንገድ ማንሳት ተገቢ ነው።

ከ100 ዓመት በፊት ያነሳቸው ችግሮች ዛሬም በዛ እንዳሉ ቢገነዘብ፤ በመፍትሔነት ያቀረባቸው ጥልቅ ዕይታዎችና አቅጣጫዎች አንዳቸውም ሥራ ላይ አለመዋላቸውን ሲያረጋግጥ ደግመን ደጋግመን እንደገደልነው ተሰምቶት ክፉኛ የሚያዝንብን ይመስለኛል። ታላቁ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ሰው ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ከ100 በፊት የለያቸው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ዛሬም በሀገራችን እንዳሉ ናቸው። በመፍትሔነት ያስቀመጣቸው ነጥቦችም አንዳቸውም ሥራ ላይ ባለመዋላቸው ከድህነትና ኋላቀርነት አዘቅት መውጣት እንዳንችል አድርጎናል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ሀብታሙ ግርማ በአንድ መጣጥፋቸው እንደገለጹት፣ “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” የሚለው መጽሐፍ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎቹ የሰው ልጅ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ሥር ማዋል እንደሚችል፣ የዓለም ሕዝቦች በሀብት ደረጃቸው እንዲራራቁ መንስዔው ጦርነት እንደሆነ፣ ጦርነት ያልነቃና ያልሠለጠነ ሕዝብ መገለጫ እንደሆነ ያብራራሉ። በኢትዮጵያም ሕዝቡ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዳይደርስ ያደረገው ጦርነት ነው ሲሉ ይሞግታሉ። ከ100 ዓመት በፊት ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ፤ የሰው ልጅ ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር ማድረግ ካልቻለ የተፈጥሮ ሎሌ ባሪያ ይሆናል እንዳለው እኛም ሎሌ ነን። የሰማይ ግት ሲነጥፍ ለድርቅ ለረሀብና ለቸነፈር የምንጋለጥ የተፈጥሮ ሎሌ።

የዓለም ሕዝቦች በሀብት ደረጃቸው እንዲራራቁ መንስዔው ጦርነት እንደሆነ ቢያስጠነቅቀንም ዛሬም የጦርነትንና የግጭትን ቀለበት ሰብረን መውጣት አልቻልንም። ከ100 ዓመት በፊት ነጋድረስ፣ “በኢትዮጵያም ሕዝቡ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዳይደርስ ያደረገው ጦርነት ነው ብሎን ሳያበቃ ዛሬም ጦርነት ላይ መሆናችንን ከመቃብሩ ቀና ብሎ ቢያየን እንዴት ያፍርብን። እንዴት ያጥርብን። በሀዘን አደባባይ ወጥቶ ልብሱን ቀዶ፤ በጸጉሩ ላይ ትቢያ እየነሰነሰ፤ በብግነት ጥርሱን እያፏጨ እንዴት ዓይኑን እንደሚያጉረጠርጥብን ሳስብ የመጽሐፉ 100ኛ ዓመት ልደት ልግጫ ቧልትና ምጸት ይሆንብኛል።

እውነት ለመናገር በሀገራችንና በሕዝባችን ያልገለጥነውን ያልተረጎምነውን መጽሐፍ ልደት ከምናከብር ለዚች ሀገርና ለዚህ ሕዝብ የነበረውን ራዕይና መሻት ዳር ባለማድረስ ከአንድም ሁለት ሶስት ጊዜ የገደልነውን የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝን ሙት ዓመት ብናከብር አይሻልም ትላላችሁ። የግል ትዝብቴን በዚህ እልባት ልስጥና እናንተም የራሳችሁ ዕይታ እንዲኖራችሁ የአማርኛው ሪፖርተር ጋዜጣ በዚያው ሰሞን ይዞት የወጣውን የ100ኛ ዓመት ዘካሪ ጹሑፍ ላጋራችሁ።

ይህ ሐሳዊ የምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚክስ) ትንታኔ ይዘት ያለው መጽሐፍ የታተመበትን 100ኛ ዓመት በማስመልከት የካቲት 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ የሥነ ጥበብ ማዕከል የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ነበር። በመድረኩ ዳሰሳ ያቀረቡት፣ የገብረ ሕይወት የኢኮኖሚ ዕሳቤዎችን ከዘመናዊ የምጣኔ ሀብት ሳይንስ፣ የንግድ ንድፈ ሃሳቦች (ቲዮሪ) እና አስተምህሮዎችን ጋር አነፃፅረው መጽሐፍ ያዘጋጁት ዓለማየሁ ገዳ (ፕሮፌሰር) ናቸው። “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳር” በዘመናዊ የምጣኔ ሀብት ጥናትና ምርምር ውስጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በማስተዋወቅና በጀማሪነት ከሚጠቀሱት በርካታ የንድፈ ሃሳብ አመንጪዎች (theoreticians) አኳያ በርካታ ሃሳቦችን አስቀድሞ የበየነ መጽሐፍ እንደነበረ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ አስረጅና እማኝ በመጥቀስ አብራርተዋል።

“መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” በዘመናዊ የምጣኔ ሀብት ጥናትና ምርምር ውስጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በማስተዋወቅና በጀማሪነት ከሚጠቀሱት የንድፈ ሃሳብ አመንጪዎች አኳያ በርካታ ሃሳቦችን አስቀድሞ የበየነ መጽሐፍ እንደነበር ዓለማየሁ (ፕሮፌሰር) አስረጅና እማኝ በመጥቀስ አብራርተዋል። በመጽሐፋቸው ውስጥ ለዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ጠቃሚና ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ፣ ሊሠራባቸው የሚችሉና በምጣኔ ሀብት ዙሪያ ያጠነጠኑ ነጥቦች መካተታቸው ከእነዚህም መካከል በበለፀጉና ባላደጉ ሀገሮች መካከል የሚከናወነው የንግድ ልውውጥ እንደሚገኙበት አስረድተዋል።

በዚሁ የንግድ ልውውጥ የበለፀጉ ሀገሮች በፋብሪካ የተመረቱ ዕቃዎችን ላላደጉ ሀገሮች ሲያቀርቡ፣ ያላደጉ ሀገሮች ደግሞ ለበለፀጉ ሀገሮች ጥሬ ዕቃዎችን በማቅረብ እንደሚንቀሳቀሱ፣ ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ደግሞ የበለፀጉ ሀገሮችን ትርፋማ እንዳደረጋቸው ነው ያመለከቱት።

ባላደጉ ሀገሮች የሚታው ግጭት/ጦርነትና ስግብግብነት ለኋላቀርነታቸው ምክንያት መሆኑንም በጽሑፋቸው ውስጥ ማካተታቸውን፣ ይህም ምክንያት ከበለፀጉ ሀገሮች ጋር እየተካሄደ ካለው የተዛባ የንግድ እንቅስቃሴ፣ ጋር ተዳምሮ ያላደጉ ሀገሮች ገቢ እያሽቆለቆለና በድህነት አረንቋ ውስጥ እንዲዘፈቁ ማድረጉንም አውስተዋል። በዚህም የተነሳ ያላደጉ ሀገሮች ገቢ ዓመት ከዓመት አንድ እየቀነሰ፣ ተስፋቸው እየተመናመነ መምጣቱን መጽሐፉ ማመልከቱን፣ ከዚህም ሌላ የኢኮኖሚ ዕድገት ከዋነኞቹ መለኪያዎች/መሥፈርቶች መካከልም የዕድገቱ ሥርጭት በኅብረተሰቡ አኗኗርና ወርሃዊ ገቢ ላይ ለውጥ ማምጣት አለበት የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ መሞከሩን ከአቅራቢው ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል።

ገብረ ሕይወት በሀብት ምጣኔ ዙሪያ የሚያራምዱት ንድፈ ሃሳብ “ሌበር ቲዎሪ” እንደሚባል ከጽሑፋቸው ለመረዳት እንደተቻለ፣ በዚህም ቲዎሪ መሠረት ከፋብሪካ እየተመረተ ለሸያጭ የሚቀርበው አንድ ዕቃ ዋጋ የሚወጣለት ዕቃውን ለማምረት የፈሰሰው የሰው ጉልበትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆኑን አንጸባርቋል። አሜሪካ ውስጥ በቅርቡ የወጣው “ሞደርን ሞኒተሪ ቲዎሪ” መንግሥት ለሕዝብ አገልግሎት የሚውል መንገድ፣ ጤና ተቋም ወዘተ ለማሠራት ከፈለገ “በጀት” የሚባል ገደብ ሳያስፈልገው ገንዘቡን እያተመ በማውጣት ብቻ ሊጠቀምበት እንደሚገባ ያስቀምጣል። ሌሎች ወገኖች ደግሞ የመንግሥት ወጪ ከገቢው ጋር እኩል ወይም የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት ያምናሉ። በጣም የሚገርመው ነገር ቢኖር የሞደርን ሞኒተሪ ቲዎሪና ፈረንጆች በልማት ኢኮኖሚ ውስጥ አገኘን ያሉትን ሌላ ቲዎሪ፣ ገብረ ሕይወት ከ100 ዓመት በፊት በተዘጋጀውና ሂሳዊ የምጣኔ ሀብት ይዘት ባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዳንፀባረቋቸው ከዓለማየሁ ገዳ (ፕሮፌሰር) ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል።

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት የተወለዱት በትግራይ ዓድዋ ሲሆን፣ በስምንት ዓመት ዕድሜያቸው ድንገት በመርከብ ወደ ባህር ማዶ ተሻገሩ። በዚያም ኑሯቸውን አድርገው ጀርመን በሚገኘው በርሊን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ተከታትለዋል። ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የጀርመን ሐኪሞች አፄ ምኒልክን ለመርዳት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ነጋድራስም በረዳትነት ተከትለዋቸው እንደመጡ፣ ነገር ግን አማርኛና ትግርኛ ስለረሱ የመግባቢያ ችግር እንደገጠማቸው፣ በዚህም የተነሳ ሰሜን ሸዋ አቶ ይገዙ በተባሉ ሰው ቤት አማርኛ ለሰባት ወራት መማራቸው ተገልጿል።

ከአማርኛ ትምህርታቸው በኋላ በሐረርና በድሬዳዋ የጉምሩክ ኃላፊ ሆነው እንዳገለገሉ፣ ‹‹አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ››፣ እንዲሁም ‹‹መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር›› የሚባሉ መጻሕፍትን እንዳዘጋጁ ገልጸው፣ የመንግሥቱን ሥራ ያከናወኑትና መጻሕፍቱንም ያዘጋጁት ለሰባት ወራት ያህል በተማሩት አማርኛ መሆኑንና ይህም ሆኖ ግን ጽሑፋቸውና ሥራቸው ዘመን ተሻጋሪና የተዋጣለት መሆኑንም አስረድተዋል። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በሕይወት ዘመናቸው በሥራቸው ጥንቁቅ፣ በአነጋገራቸው ደፋር እንደነበሩና በዚህም የተነሳ ከጊዜው ሰዎች ጋር እንደማይስማሙ ነው የተገለጸው።

በነካ እጄ ሰሞኑን ያነበብሁትን በዶ/ር ሩቅያ ሀሰን የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የሥነ ልሳንና ሥነ ተግባቦት ተባባሪ ፕሮፌሰር የመጽሐፍ ቅኝት ወይም የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን ቡክ ሪቪው ወይም የመጽሐፍ ግምገማ ላጋራችሁ። የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝን ሁለት መጽሐፎች በአንድ ጥራዝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በ2003 ዓ.ም. አሳትሞታል። የነባር ምርጥ መጻሕፍት ሕትመት በሚል ርእስ እያሳተማቸው ካለው መጽሐፎች ውስጥ ይህ ድንቅ ሥራ በመካተቱ ፕሬሱ ሊመሰገን ይገባል። በዚህ መጽሐፍ በአንድ ጥራዝ የወጡት የነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች “አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ”ና “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” የተሰኙ ናቸው። ሥራዎቹ እንዲታተሙ ሃሳብ ያቀረቡት የወቅቱ የፕሬሱ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለ እንደሆኑ የየነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ የልጅ ልጅ የሆኑት ወ/ሮ ዓይናለም አሸብር ገብረ ሕይወት ገልጸዋል።

ለመጽሐፉ መግቢያ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንዲሁም ፕሮፌሰር አለማየሁ ገዳ ጽፈዋል። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በመጽሐፉ ጀርባ ላይም እንደታተመው ስለደራሲው ሁለት አስገራሚ ነገሮችን ሲጠቅሱ አንደኛው ገብረ ሕይወት ይህን የመሰለ እስካሁን ድረስ የሚያስተጋባ ጥልቅ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ጉዳዮችን በሰላሳዎቹ እድሜ መጻፍ መቻላቸውና ሁለተኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባልሆነው በአማርኛ ውብና አጥንት የሚሰረስር ሥራ ጽፈው ማለፋቸው ነው። የሞቱት በ33 ወይም በ37 ዓመት እድሜያቸው በ1911 ከአውሮፓ በመጣው የንፋስ (ግሪፕ) የወረርሽኝ በሽታ እንደሆነ በመጽሐፉ ተገልጿል።

ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳ በሁለተኛው መጽሐፍ ላይ ሰፋ ያለ አድናቆት ያስቀመጡ ሲሆን የብዙ ኢኮኖሚክስ ሃሳቦች ባለቤት እንደነበሩና ከሳቸው ከ50ና 60 ዓመት በኋላ የመጡ ምእራባውያን ኢኮኖሚስቶች የሳቸውን ሃሳብ በባለቤትነት ወስደው እንደሚታወቁበት ነገር ግን አሁንም የነጋድራስ ሞዴል እያሉ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳ የሚጠሯቸው አዳዲስ የኢኮኖሚክስ ሃሳቦች እንዳሏቸው በከፍተኛ አድናቆት ጽፈዋል።

ሻሎም ! አሜን።

# ወቅታዊ

# ‹‹አሠሪዎችና ሠራተኞች በውይይት ችግሮቻቸውን ሲፈቱ ሰላሙ የተረጋገጠ ምርታማ ኢንዱስትሪ ይፈጠራል››

- አቶ ካሣሁን ፎሎ
የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት



**ስምስም መንግሥቱ**

በሥሩ 2ሺ303 ተቋማት ወይም ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የተቋቋሙ ሠራተኛ ማህበራትና ወደ አንድ ሚሊየን የሚደርስ አባላት ያለው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) የሠራተኞችን በነፃነት የመደራጀት፣ መብትና ጥቅሞቻቸውም እንዲከበሩላቸው እየሠራ ያለ ተቋም ነው። ይዞ የተነሳቸው ዓላማዎቹን ለማሳካት ምን ያህል ርቀት እንደተጓዘ፣ ስኬቶቹን፣ የኢንዱስትሪው ሰላምና መረጋጋት በምን ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ከኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ ጋር ያደረግነው ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በየዓመቱ እየተከበረ ስላለው ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን (ሜይዴይ) መነሻና ፋይዳው ያስታውሱን?**

**አቶ ካሣሁን፡-** ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀንን ለማክበር መነሻ የሆኑት፤ ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ በሠራተኛ ላይ የሚደርሱ በደሎች፤ ያለረፍት ለረጅም ሰዓት መሥራት፣ የደመወዝ ክፍያ አነስተኛ መሆን፣ የሙያ ደህንነት አለመጠበቅና የዓመት ዓረፍትም አለመኖር ዋነኞቹ ናቸው። ጉዳት ሲደርስባቸውም የጉዳት ካሳ አለማግኘት እና በደል ደርሶባቸውም የሚያሰራቸው ኩባንያ ያለምንም ካሳና ክፍያ ሲያባርራቸው መቆየቱም ሌላኛው ምክንያት ነው።

እንዲህ ያሉ በአሠሪዎች የሚደርሱ በደሎችን ለመቃወም ሠራተኞች እንቅስቃሴ ጀመሩ። እንቅስቃሴው የተጀመረውም በኢንዱስትሪ በበለፀጉ ሀገሮች ሲሆን፤ ፊር ቀዳጆቹ በአሜሪካን ሀገር ውስጥ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ናቸው። በሂደት ወደ ካናዳ፣ አውሮፓና ሌሎች ሀገሮች እንቅስቃሴው ተዛምቶ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች በተለያየ መልኩ ትግላቸውን ሲያካሂዱ ቆዩ።

ሠራተኛ ማህበር የሚመስል ግን ደግሞ እውቅና የሌለው ማህበር አቋቁመውም ነበር። ቆይተው ደግሞ የጋራ የሆነ ህብረት መፍጠር ሞከሩ፤ ሠራተኞች ከሚደርስባቸው ጭቆና ለመውጣት፤ እ.ኤ.አ በ1884 የሥራ ማቆም ርምጃ ወሰዱ። ብዙ ትግልም አደረጉ። ሆኖም ግን የሥራ ማቆም ርምጃው ሕጋዊ የሆነ ሽፋን አልነበረውም። ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ የነበረው፤ የሥራ ማሽኖችንም በመስበር ጭምር ነበር ።

ይወስዱ በነበረው የኃይል ርምጃ፣ ሠራተኞችን አደራጅታችኋል፣ አስተባብራችኋል በሚል ብዙዎች ታሰሩ። በአደባባይ በስቅላት እንዲቀጡ የተወሰነባቸውም ነበሩ። ለመብታቸው ሲታገሉ እንዲህ የተለያየ በደል የደረሰባቸውን ሠራተኞች ለማሰብ እ.ኤ.አ በ1886 ሜይ አንድ ቀን በካናዳና በአፍሪካ ያሉ ሠራተኞች የጋራ ጉባኤ አካሄዱ። ጉባኤው በአደባባይ ላይ የተሰቀሉ ሰዎች እንዲዘከሩ ውሳኔ አሳለፈ። በዓሉ በየዓመቱ ሜይ አንድ ቀን መከበር የጀመረው ግን እኤአ በ1890 ጀምሮ ነው።

የበዓሉ ዓላማም፤ ለሠራተኞች መብት ሲታገሉ መስዋዕት የሆኑ ሰማዕታትን ማሰብና ለወደፊቱ ደግሞ የትግል ቃል ኪዳንን ለማደስ ነው። በተጨማሪም በዓሉ በየዓመቱ ሲከብር ሠራተኞች ያሉባቸው ችግሮች ጎልተው እንዲወጡ ይደረጋል። በዓሉ መከበር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ሀገራት በተለያዩ መሪ ሃሳቦች ሲከበር ቆይተዋል። የዓለም የሠራተኞች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከበር ዘንድሮ ለ135ኛ ጊዜ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ49ኛ ጊዜ ነው።

የበዓል አከባበርም እንደየሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ይለያያል። አንዳንድ ሀገራት በፌስቲቫል ደረጃ በማዘጋጀት ሳምንቱን በሙሉ በተለያየ ዝግጅት ያከብራሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ባላቸው ወቅታዊ ችግር ላይ አደባባይ ወጥተው ተቃውሞ ያሰማሉ። ቀኑን ምክንያት በማድረግ በአዳራሽ ውይይት በማካሄድ የሚያከብሩም አሉ።

የሜይዴይ መከበር ፋይዳውን ስናነሳ ደግሞ፤ የሠራተኞች እንቅስቃሴ ሲጀመር፤ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙት አደባባይ በመወጣት ነበር። ዛሬ ስለዓለም ሥራ ድርጅት የምናወሳው፣ አሰሪ፣ ሠራተኛና መንግሥት በጋራ ሆነው ማህበራዊ ምክክሮሽ ደረጃ ላይ መድረስ የቻለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በነበረው ትግል ነው። ትግሉ ገፍቶ በዓለም አቀፍ ደረጃም የመሰባሰብ ሁኔታ መጣ። በጣሊያን በፈረንሳይ፣ በእንግሊዝ፣ በጀርመን በሁሉም ሀገራት ትግሎች ነበሩ።

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እ.ኤ.አ. በ1919 ትኩረት የተሰጠው፣ የሠራተኞች ጉዳይ በሰላማዊ ሁኔታ ካልተፈታ በየትኛውም ዓለም ሰላም ሊኖር አይችልም ተብሎ ነበር። ከዚሁ ጎን ሊግ ኦፍኔሽን ተቋቁሞ ነበር። የማቋቋሙ ሃሳብ የተነሳው ከአሜሪካን ነው። የአሠሪ፣ የሠራተኛና የመንግሥት ግንኙነት የሚመራ አንድ ዓለም አቀፍ ተቋም መኖር እንዳለበትም በሊግ ኦፍኔሽን ውይይት ተደረገበት።

እ.ኤ.አ. በ1919 በተባበሩት መንግሥታት ሥር ሆኖ የሚሠራ የዓለም የሥራ ፓርላማ ተቋቋመ። በዓመት አንድ ጊዜ አሰሪ፣ ሠራተኛና መንግሥት በየሀገራቱ የሚወያዩበት እንዲሆን ለማስቻል ነው። ይህ ድርጅትም እንዲፈጠር ያስቻለው ሠራተኞች ያደረጉት ትግል ነው።

ወደ ዘንድሮ ሜይዴይ አከባበር ለመመለስ፤ በተለይም የኢትዮጵያን ጉዳይ ስናነሳ ኢንዱስትሪው ወደኋላ ቀርቶ የጀመርን ቢሆንም፤ በሌሎቹ ሀገሮች የደረሱት ጭቆናዎች በሀገራችንም ደርሷል። በሀገራችን ኢንዱስትሪዎች ማቆጥቆጥ የጀመሩት ኢትዮጵያን በኃይል የወረረው ፋሽስት ጣሊያን ከሀገር ከወጣ በኋላ ነው። አብዛኞቹም ፋብሪካዎች በንጉሣውያን ቤተሰቦች የተያዙ ናቸው።

በዚህ ምክንያትም በሠራተኞች ላይ ከፍተኛ ጭቆና ይደርስ ነበር። ጭቆናው እንዲባባስ ያደረገው ደግሞ በወቅቱ የባሪያ ሽያጭ የነበረበት የፊውዶ ቡሩዣ ሥርዓት ስለነበረ ነው። ይህ ሥርዓት ቢለወጥም ኢንዱስትሪው ውስጥ የነበረው የአሽከርና ሎሌ ዓይነት እንጂ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አልነበረም። በወቅቱ ሠራተኛ ማህበር ማቋቋም ወንጀል ነበር። ይህን ችግር ለማስወገድ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አማራጭ ያደረጉት በየፋብሪካው ውስጥ እድር ማቋቋም ነበር። ቆይተው ደግሞ ሀገር አቀፍ የሠራተኞች መረዳጃ እድር ብለው ከፍ አደረጉት።

እድሩን የሚመራም መረጡ። ውይይት ሲያደርጉም ያነሱ የነበረው የሥራ ሰዓት መቀነስ እንዳለበት፣ በሌሎች ሀገሮች እንደተደረገው ሁሉ በነፃ የመደራጀት መብታቸው እንዲጠበቅ፣ የሙያ ደህንነታቸውና ጤንነታቸው መጠበቅ እንዳለበት፣ ደመወዛቸው እንዲስተካከል ነው። እነዚህን መብቶቻቸውን እያነሱ የሚወያዩትም በየቤተክርስቲያኑ ውስጥ እና በግለሰቦች ቤት ውስጥ በመገናኘት ነበር።

መረዳጃ እድሩ እያስተባበረ ውስጥ ለውስጥ ትግል ማድረጉ ተጠናክሮ ወደ ሥራ ማቆም ርምጃ ተሸጋገሩ። በ1954 ዓ.ም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ይቋቋም የሚል ሃሳብ ተነሳ። ይሁን እንጂ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የሌላት ሀገር እንዴት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይቋቋማል? የተሻልን እኛ ነን የሚል ከተለያዩ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ተቋውሞ ተነሳ። በወቅቱ ኢትዮጵያን ይመሩ የነበሩት ንጉሥ አፄ ኃይለሥላሴ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመራ ደንብ በ1954ዓ.ም እንዲወጣ አደረጉ።

ደንቡ ግን ዝርዝር አልነበረም። ደንቡን መሠረት አድርጎ በ1955ዓም ሀገር አቀፍ የሠራተኞች ማህበር እንዲቋቋም ተደረገ። እድሩን ሲመሩ የነበሩት ማህበሩንም እንዲመሩ ተደረገ። መሪዎቹም በዓለም አቀፍ ሠራተኞች ኮንፌዴሬሽን ስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ስልጠና ተሰጣቸው። ወደ 29 የሚሆኑ ማህበራት የነበሩ ሲሆን፤ የራሳቸውን ምርጫ በማድረግም ከሚያዝያ አንድ ቀን 1955 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር (ኢሠአማ) መሠረቱ።

ሠራተኞቹ ማህበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ወታደራዊ የደርግ አገዛዝ ሥልጣኑን እስኪረከብ ድረስ ከፍተኛ ትግል ሲያደረጉ ነበር። ከሠራዊቱና ከተማሪዎች ቀጥሎ የሠራተኛው ትግል በሶስተኛ ደረጃ የሚገኝ ነበር። በአስመራ፣ በድሬዳዋ፣ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪዎች ባሉባቸው ሁሉ በተከታታይ የሥራ ማቆም አድማዎች ይደረጉ ነበር። በወቅቱ የሠራተኛውን መብት ለማስከበር እድር እንዲቋቋም ሃሳብ ከማፍለቅ ጀምሮ በመሪነት ጭምር ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ አቶ አበራ ገሙ የተባሉ ሰው አይዘነጉም።

ማህበሩን እንዲመሩ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተመረጡት አቶ አብረሃም መኮንን ፕሬዚዳንት ሲሆኑ፤ አቶ አበራ ገሙ ደግሞ የማህበሩ የክብር ፕሬዚዳንት ሆነው በማማከር ያግዙ ነበር። ሆኖም ማህበሩ በሚፈለገው ልክ ሥራውን ለመሥራት ባለመቻሉና የመንግሥትንም ድጋፍ ባለማግኘቱ አቶ አበራ ገሙ ያለውን ሁኔታ መቋቋም ባለመቻላቸውና የሚሆነውም ማየት ባለመፈለጋቸው እራሳቸውን ለማጥፋት ችለዋል። ግለሰቡም እየታወሱ ይኖራሉ።

ወታደራዊው ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ቢሆን፤ ምቹ ሁኔታ አልነበረም። ሀገርን የተቆጣጠረው የወታደሩ ክፍል ነበር። የሠራተኛ ማህበሩ የሠራተኛ ፓርቲ ይባል ነበር። በስፋት የፓርቲ ሥራዎች ይከናወኑበት ነበር። ሜይዴይ እስከዚህ ድረስ አልተከበረም። በኢትዮጵያ ሜይዴይ መከበር የጀመረው በ1968 ዓ.ም ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ሕዝቡ የሚያከብረው በቀበሌ ታዞ ሰልፍ እየወጣ ነበር። ርእሰ ብሔሩም በስፍራው ተገኝተው ንግግር ያደርጉ ነበር።

ሜይዴይን የምናከብረው ለሠራተኞች መብትና ጥቅም ብለው በመታገላቸው ሥራ እንዲለቁ የተወሰነባቸውን፣ የታሰሩትንና እራሳቸውንም ያጠፉትን በማሰብ፣ ለቀጣይም ቃል ኪዳናችንን በማደስ ነው። ሌሎች ወቅታዊ የሆኑ ጥያቄዎችም በዓሉን መሠረት አድርገው ይነሳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ አሁንም በኢንዱስትሪው አላደገችም። በኮንፌዴሬሽን ደረጃ የሠራተኛ መብትን ለማስከበር የሚደረገው እንቅስቃሴ ምን ያህል ውጤታማ ነው?**

**አቶ ካሣሁን፡-** መሠረታዊ ማህበራት አሉ። በክፍለ ኢኮኖሚ ደረጃ ደግሞ የተደራጁ ፌዴሬሽኖች አሉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ኮንፌዴሬሽን አለ። ስለዚህ በ1955 ዓ.ም ማህበር ሲቋቋምም ሀገር አቀፍ ነበር። ኢንዱስትሪ ከዘመነ ወይንም ካደገ በኋላ ኮንፌዴሬሽን ይሆናል የሚል አካሄድ የለም። ኮንፌዴሬሽን የሚወክለው ሀገርን ነው። በዓለም ሥራ ድርጅት ለመወከልም ሆነ ከመንግሥት ጋር ለመነጋገር ሀገር አቀፍ ማህበር ያስፈልጋል።

የኮንፌዴሬሽኑ ዋና ተግባር በሀገር አቀፍ በሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ላይ ከመንግሥት ጋር ድርድር ያደርጋል። ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ከመቅረቡ በፊት ቅድሚያ የሚነጋገሩት አሠሪ፣ ሠራተኞችና መንግሥት ናቸው። የሶስትዮሽ ምክክር ወይም መድረክ የሚያስፈልገው በጋራ እየተመካከሩ ልዩነቶቻቸውን እያጠበቡ ወደ አንድ እንዲመጡ በማሰብ ነው። የተወሰነ ልዩነት ካላቸው ደግሞ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተልኮ የሚያስታርቅ ውሳኔ ያሳልፋል። ውሳኔም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተልኮ ይፀድቃል። ኮንፌዴሬሽን አስፈላጊ የሚሆነው ከዚህ አኳያ ነው።

ታች ያሉት ከአሠሪው ጋር የሚደራደሩት እንደየድርጅታቸው ባህሪና የህብረት ስምምነት ነው። ችግር ሲያጋጥማቸው የሚያግዛቸውና የሚከራከርላቸው ኮንፌዴሬሽኑ ነው። የሕግ ድጋፍም ያደርግላቸዋል። ስልጠና ይሰጣቸዋል። ኮንፌዴሬሽኑ እስከ ዓለም አቀፍ ድረስ የተደራጀ ነው። በአፍሪካ ደረጃ የሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የዓለም አቀፍ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን አለ። ኮንፌዴሬሽኑ ግንኙነቱ ዓለም አቀፍ ነው። የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ሲወጣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ ብቻ አይደለም፤ ለሠራተኞች የተቀመጡ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ደረጃዎች አሉ። ሀገራት የሚያወጡት ሕግ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓለም ሥራ ድርጅት ከወጡ ድንጋጌዎች በታች መሆን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ከገጽ 7 የዞረ

## ‹‹አሠሪዎችና ሠራተኞች በውይይት...

የለበትም። በአጠቃላይ የሠራተኛ ጉዳይ ዓለም አቀፍ ባህሪ አለው።

**አዲስ ዘመን፡- ኮንፌዴሬሽኑ እስከ አሁን ባከናወናቸው ተግባራት በስኬት የሚያነሳቸውንና ተግዳሮቶችንም ቢያብራሩልን?**

**አቶ ካሣሁን፡-** የኮንፌዴሬሽኑ ዋና ተግባራት የሠራተኛውን መብትና ጥቅም ማስከበር ነው። በመሆኑም በመጀመሪያ ሠራተኛው ለመብትና ጥቅሙ እንዲታገል በማህበር እንዲደራጅ ማድረግ ሲሆን፤ ለዚህም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል። የሠራተኛው መብትና ጥቅም፤ ያለበትን ችግርም ሆነ ከሠራተኞች፣ ከአሠሪዎችና ከመንግሥት ጋር በድርድር እንዲፈታለት ይደረጋል። በመሠረታዊ ደረጃ ያሉ አመራሮችም ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ። ከእነርሱ በላይ ሲሆን ደግሞ በክፍለ ኢኮኖሚ ለተደራጁ ፌዴሬሽኖች ይቀርባል።

እነርሱም ከአቅማቸው በላይ ሲሆን፤ ለኢሠማኮ ወይም ለኮንፌዴሬሽን ያስተላልፋሉ። ኮንፌዴሬሽኑ ደግሞ በድርድር እንዲፈታ ማድረግ ካልቻለ ወደ ሕግ በመውሰድ እስከ ሰበር ሰሚ ድረስ ለሠራተኛው ተከራክሮ መፍትሔ እንዲያገኝ ያደርጋል። የማህበር አባል የሆነ ሰው ነፃ የሕግ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው። የኮንፌዴሬሽኑ ቅርጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ባሉበት ሁሉ የሕግ ባለሙያዎች ስላሉ የሕግ አገልግሎት ይሰጣል።

የሠራተኛ የመብትና የተለያዩ ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ መፍትሔ ተሰጥቷቸው የሚያቆሙ አይደሉም። ለምሳሌ የደመወዝ ጥያቄ አንዴ ተጨምሮ ይበቃል የሚባል አይደለም። ኑሮ ተለዋዋጭ በመሆኑ የደመወዝ ጥያቄ ይቀጥላል። አሠሪው ከሚያገኘው ትርፍም ለሠራተኛው መስጠት ይኖርበታል። በዚህ ላይ ሠራተኛውና አሠሪው መደራደር አለባቸው። ድርድሩ ቀላል አይሆንም። በተለይም አሠሪው ላለመክፈል ብዙ ውጣውረድ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። ውል ተፈራርመው እንኳን ተፈፃሚ አያደርጉም። ኮንፌዴሬሽኑ የቆመው ለሠራተኛው በመሆኑ እነዚህን ነገሮች ይከታተላል። እንዲህ ያሉ ነገሮች ማቆሚያ ስለሌላቸው ችግሩ አንዴ ብቻ አይፈታም።

ኮንፌዴሬሽኑ ውጤት ካስመዘገበባቸው አንዱ፤ በግል ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የሥራ አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ ጡረታ የማግኘት መብት አልነበራቸውም። ኮንፌዴሬሽኑ ከብዙ ትግል በኋላ በግል ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በ2003 ዓ. ም የጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው ማድረግ ችሏል። ሌላው በ2008 ዓ.ም የሥራ ግብር ተቀንሷል። ይህ ውሳኔ ሲወሰን በደመወዝ ተከፋዩ ላይ የኑሮ ጫና ነበር።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥናት ተጠንቶ ለሁሉም ደመወዝ ተካፋይ ሠራተኛ የሥራ ግብር ቅናሽ ሊደረግ ችሏል። የወሊድ ፈቃድም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥና በግል ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ልዩነት ነበረው። እኩል መሆን አለበት የሚል ጥያቄ አቅርበን ነበር። በተለየ ሕግ ይተዳደሩ የነበሩ የኤጀንሲ ሠራተኞች ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መታቀፍ አለበት የሚል ጥያቄም በማቅረብ ብዙ ተከራክረናል።

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንድ ሰው በዓመት ዓረፍት የሚሰጠው 14ቀን ብቻ ነበር። በግል ሠራተኞች ግን የተቀመጠው ሰባት ቀን ብቻ የሚል ነበር። እርሱም ቢሆን አሠሪው ሲፈቅድ የሚል ነው። ሠራተኛው በተለያየ ምክንያት አንድ ቀን ከቀረ ሁለት ቀን ካረፈደም ከሥራው ይባረራል፤ የሥራ ስንብት ክፍያም ማግኘት የለበትም የሚሉና ሌሎችም ጫናዎች ነበሩት። እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ነበሩ። በመቀጠል ያደረግነው ልዩነቶቻችን አስመልክቶ ሠራተኛውን የማስተባበር ሥራ ነው የሠራነው። ኮንፌዴሬሽኑ ነገሮች እንዲቀየሩ ሠራተኛውን የማስተባበር እንጂ ሌላ ነገር ማድረግ አይችልም። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅም ሆነ በሕገ መንግሥቱ በተፈቀደው መሠረት ሕጋዊ መንገድ ተከትሎ ሰላማዊ ሠልፍ በማድረግ፣ ሥራ የማቆም ርምጃ መውሰድ ነው። እነዚህን መብቶቹን የሚጠቀመው ግን የመጨረሻ አማራጭ ላይ ሲደርስ ነው።

በ2011 ዓ.ም በወጣው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የዝቅተኛ ደመወዝ ወለል ከወቅቱ የገበያና ኢኮኖሚ ጋር በማየት በየዓመቱ የሚከለስ የደመወዝ ቦርድ ይቋቋማል የሚል ውሳኔ ላይ መድረስ ተችሏል። ይሁን እንጂ ዝቅተኛ የደመወዝ የወለል መጠን በሕግ ባለመወሰኑ ጥያቄው ቀጥሏል። ኮንፌደሬሽኑ በሕጎች፣ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ይከራከራል፤ ይደራደራል፣ ሠራተኞችንም ያስተባብራል።



**አዲስ ዘመን፡- የሠራተኞች የመደራጀት መብትን የሚጥሱ የግል አሠሪ ድርጅቶች ላይ ቅሬታ ይነሳል። ይህን የሚፈጽሙት ዓለም አቀፍ ሕጉን ጠንቅቀው የሚያውቁ የውጭ ኩባንያዎች ጭምር ናቸው። በእናንተ ግምገማ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ካሣሁን፡-** የሠራተኛው ጥያቄ በአንዴ የሚያበቃ አይደለም ያልኩት ለዚህ ነው። እንዲህ ያለው ችግር የሚስተዋለው በውጭም በሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጭምር ነው። ከተደራጀ ጥቅሙን ይጠይቀኛል ከሚል ነው። ሠራተኛው የሚጠይቀው በአዋጅ የተፈቀደለትን ነው። አንዳንዶቹ ጥያቄዎች ማህበር ኖረም አልኖረም መሟላት ያለባቸው ናቸው። ለምሳሌ የደህንነት መጠበቂያ አልባሳትና ተያያዥ ነገሮች ያስፈልጋሉ። አሠሪዎች ይሄንን እንደ ወጪ ይቆጥሩታል። ካደጉ ሀገራት የመጡት ኩባንያዎችም ቢሆኑ ካልተገደዱ በስተቀር ለማሟላት ፈቃደኛ አይሆኑም። ለምሳሌ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ሠራተኞች መደራጀት አይችሉም ነበር። እኔም እዛ ግቢ መግባት አልችልም ነበር። ከተለያዩ የመንግሥት ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከአሠሪዎች ጋር በመወያየት፣ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል።

ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በማህበር ተደራጅተዋል። ቦሌ ለሚ ውስጥ የሚገኝ አንድ ድርጅት ቀርቶ ነበር። አሁን እነርሱም ፈቃደኛ ሆነዋል። ዱከም ኢንደስትሪ ዞን ውስጥ ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ኢንደስትሪዎች አሉ። ግን አንድም ሠራተኛ በማህበር አልተደራጀም። ክትትላችንን እንቀጥላለን። እነዚህ ያነሰኋቸው በአንድ አካባቢ ያሉትን ነው። በተለያየ ቦታ ያልተደራጁ አሉ። አዲስ የሚመጣውም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያልፍ ነው። ስለዚህ ሥራው ተጠናክሮ በመዋቅራዊ አካሄድ እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ /ዶክተር/ ጋርም በነፃ የመደራጀትና የመደራደር መብት ላይ ችግሮች መኖራቸውን በተመለከተ ስለ ሠራተኞች ጉዳይ ስንወያይ ነበር። ከተነጋገርንባቸው ችግሮች መካከል በሀገር አቀፍ ደረጃ በተቋቋመ አሠሪና ሠራተኛ አማካሪ ቦርድ ሥራን የተመለከተ ነው። ቦርዱ ከሠራተኛ፣ ከአሠሪና ከመንግሥት የተውጣጡ 15 አባላት የተካተቱበት ነው። በውይይታችን ቦርዱ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ሥራው ተቋርጦ ስለነበር ሥራውን እንዲቀጥል አንስተናል። የሚነሱ ጥያቄዎች ለቦርዱ ቀርበው ውሳኔ ያገኛሉ። ከውይይቱ በኋላ አማካሪ ቦርዱ ሥራውን የቀጠለ ሲሆን፣ የሚመራው በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ነው።

የ2016 ዓ.ም እቅድ ወጥቶ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ፀድቆ እየተተገበረ ነው። የመደራጀትና መደራደር ነፃነት መብትን የተመለከተ ጉዳይ በስድስት ወር አንዴ ቋሚ የሆነ መድረክ ይካሄዳል። የመደራጀት ምጣኔ ምን ያህል እንዳደገ፣ መደራጀት ለምን አነሰ፣ በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች የአፈታት ሁኔታ፣ የሚሉ ግምገማዎችን ያደርጋል። አቅጣጫዎችንም ያስቀምጣል። ሁለት ጊዜ መድረኮች ተዘጋጅተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የኢንዱስትሪው ሰላም በምን ሁኔታ ላይ ነው?**

**አቶ ካሣሁን፡-** ኢንዱስትሪው ውስጣዊም ውጫዊም ጫናዎች አሉበት። ውጫዊ ጫናው ድርጅቶች ለኢንዱስትሪው የሚሆን ጥሬ ዕቃ ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ችግር ነው። በዚህ ምክንያትም ሠራተኞች ይቀንሳሉ። አንዳንዶቹ ሠራተኛው ማግኘት የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም ይቀንሳሉ። ይሄ መረጋጋትን አይፈጥርም። ሌላው ጫና ደግሞ የፀጥታ መደፍረስ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ሠራተኞች ታግተው ገንዘብ ይጠየቃል። የሚገደሉም አሉ። ለአብነት በሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ሠራተኞች ላይ የደረሰውን ማንሳት ይቻላል። ወንጂና መተሀራ ላይም ሠራተኞች ታግተው ተገድለዋል። ይሄ ሠራተኛው እንዳይረጋጋ እያደረገው ነው። ችግሩ በተለይ በክልሎች ጎልቶ ይስተዋላል።

በውስጥ የሚደርሰው ጫና በነፃ መደራጀትና የመደራደር መብት እንዲሁም አሠሪው የገባውን ቃል አለማክበር ሲሆን፣ በዚህ ሁኔታም ግጭቶች ይፈጠራሉ። በተቻለ መጠን በውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው። ውጫዊው ጫና ግን የጋራ የሆነ እንደ ሀገር መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኮንፌዴሬሽኑ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ካሣሁን፡-** ኮንፌዴሬሽኑ የዓለም ሥራ ድርጅት አባል ነው። ከዚያ ውጭ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በተለያየ መልኩ ግንኙነት ያደርጋል። ለማህበር መሪዎች የምንሰጠውን የተለያየ ሥልጠና ከዓለም አቀፉ በምናገኘው ድጋፍ ነው። የአፍሪካ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጋር በጋራ ሆነን እንደ ሀገርም፣ እንደ አፍሪካም ስላለው ችግር እንወያያለን። የአፍሪካ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልም ነን።

በምክትል ደረጃም በምክር ቤቱ ሠርተናል። ከኖርዌይ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጋር በቅርበት እንሠራለን። በሥልጠናና በተለያየ መልኩም እያገዙን ነው። ከአሜሪካን ሌበር ፌዴሬሽን ጋርም በቅርበት እንሠራለን። የዓለም አቀፍ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ኦዲት አባል ሆነን እየሠራን ነው። ኮንፌዴሬሽኑ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በአፍሪካም በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥሩ ቅርበት እንዳለን ይታወቃል።

‹‹በአንዳንድ ሀገር ጥቁርና ነጭ በሚል ክፍፍል ይደረጋል። ኢትዮጵያ ደግሞ የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ሆና፤ አሁን ደግሞ ሀገሪቷ ውስጥ እየታየ ባለው የፖለቲካ ትኩሣት ኢሠማኮ ተጽእኖ ሳይፈጠርበት እንዴት አንድነቱን አስጠብቆ ሊቆይ ቻለ?›› ተብሎ ጥያቄ ቀርቦልን በተለያዩ ዓለም አቀፍ የጉባኤ መድረኮች ላይ ተሞክሯችንን አካፍለናል። ሠራተኞችን እንዴት እንደምናደራጅም እንዲሁ ልምድ አካፍለናል።

ሌላው የአፍሪካ ቀንድ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን የሚባል አለ። ከስምንቱ የኢጋድ አባል ሀገራት ጋር የጋራ የሆነ አንድ ኮንፌደሬሽን አለን። ችግሮቻችን ተመሳሳይ በመሆናቸው የሠራተኞች መብትና ጥቅምን ለማስጠበቅ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን መንግሥታትን ማገዝ ስላለብን፣ በተጨማሪም በአፍሪካ ቀንድ የሰዎች ነፃ ዝውውር መኖር አለበት ብለን ስለምናምን፣ መንግሥታት ኢጋድ ያወጣውን ፕሮቶኮል ስምምነት እንዲፈርሙ በጋራ ለመሥራት አንድነታችን አስፈላጊ ነው። ፍላጎታችን የምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ወደ አንድነት እንዲመጣ ነው። ኮንፌዴሬሽናችን፤ የእርስ በእርስ ጦርነት መቆም አለበት፤ ችግሮች መወገድ አለባቸው፤ ሀገሮች በሥጋት የሚተያዩበት ነገር መወገድ አለበት ብሎ የሚያምንና ለችግሮችም መፍትሔ እንዲበጅ የሚሠራ ተቋም ነው። ከኢጋድ ጋርም በቅርበት እየሠራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ኮንፌዴሬሽኑ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ያለው ሚና እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ካሣሁን፡-** ዴሞክራሲ ለሁሉም ነገር መሠረት ነው ብለን እናምናለን። በሠራተኛ ማህበራት ውስጥም የዳበረ ነው። የዴሞክራሲ ሥርዓት ግጭትን ለማስወገድ፣ እድገትን ለማምጣት ይረዳል። እንደሀገርም ባህል መሆን አለበት። ምክንያቱም ችግሮቻችንን በኃይል ሳይሆን፤ በውይይትና በንግግር መፍታት ደረጃ ላይ ለመድረስ ያስችለናል። ኮንፌዴሬሽኑ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል። የሥነ ዜጋ ስልጠናዎችን ይሰጣል። ሀገራዊ ምርጫ ሲካሄድ በታዛቢነት ይሠራል።

**አዲስ ዘመን፡- በዓሉን አስመልክቶ መልዕክት ካልዎት ያስተላልፉ?**

**አቶ ካሣሁን፡-** የሠራተኞች በነፃ የመደራጀት መብት ሠራተኛውንና አሠሪውን የጋራ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል። አሠሪዎችና ሠራተኞች በውይይት ችግሮቻችን ሲፈቱ ሰላሙ የተረጋገጠ ምርታማ ኢንደስትሪ ይፈጠራል። ድርጅቱ ከያዘው ሠራተኛ በላይ ተጨማሪ ለመቅጠር ያስችለዋል። ኢንዱስትሪው ሲስፋፋ፣ የሠራተኛውም መብት ከተጠበቀ የአባላቱ ቁጥርም ይጨምራል። ኮንፌዴሬሽኑ ለዚህ መደላድል ለመፍጠር ሪፎርም እየሠራ ነው። ኢንዱስትሪ በሚበዘባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ በመክፈት ታች ወርደን ለማጠናከር እየሠራን ነው።

በቅድሚያ ለመላው ሠራተኞች እንኳን ለሜይዴይ አደረሳችሁ ማለት እፈልጋለሁ። ‹‹ለሰላምና ለኑሮ ውድነት መፍትሔ እንሻለን።›› በሚል መሪ ቃል በምናከብረው ሜይዴይ በዓል ላይ ሌሎችም መልስ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። በተለይ ደግሞ ሰላም ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ኢንደስትሪው ምርታማ ሆኖ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ሚና እንዲኖረው ሰላም ያስፈልጋል። ሰላም ለማስፍን መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ቢሆንም፤ የሁሉም አካላት ትብብርና ተሳትፎ መኖር አለበት። ኑሮ ውድነቱም ቢሆን፤ የሚቃለልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። መንግሥት ለቀረበለት ጥያቄም መልስ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ካሣሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የኢንዱስትሪዎችን ተረፈ ምርት መቀነስና ተወዳዳሪ ማድረግ የሚያስችለው ፕሮጀክት

ሰሚራ በርሀ

ኢንዱስትሪዎች ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ምርቶችን በማምረት ይታወቃሉ። አልባሳትን፣ የሕክምና መሳሪያዎችንና መድኃኒቶችን፤ የግንባታና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን፣ ወዘተ በማምረት ዓለማችን አሁን ለደረሰችበት ከፍተኛ ደረጃ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፤ እያበረከቱም ይገኛሉ።

እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በአንጻሩ የሰው ልጅን በእጅጉ ሊጎዱ የሚችሉ ተረፈ ምርቶችን ወደ አካባቢ በመልቀቅም ይወቀሳሉ። በአየር ንብረት ላይ ለተከሰተው ብክለት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ለዚህ ደግሞ በማምረት ሂደት የሚከተሉት መንገድ እንደሆነ ይገለጻል።

አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ማምረት ቢችሉ እንደ ተወደዱ ይዘልቃሉ። ይሁንና በአብዛኛው ይህን እያደረጉ አለመሆናቸው ነው የሚገለጸው። ለእዚህም ነው አመራረታቸው አካባቢን እንዳይጎዳ ማድረግ የሚያስችሉ አሠራሮች እየተተገበሩ የሚገኙት። በኢትዮጵያም ይህን አሠራር ለመትግበር ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙበትን ፍሳሽ የሚያጣሩባቸውን ማጣሪያዎች ገንብተዋል።

በተለያዩ የዓለም ሀገራት ኢንዱስትሪዎች ተረፈ ምርቶችን የሚያጣሩባቸው መንገዶች እየተቀየሩ ይገኛሉ። ኢንዱስትሪዎቹ እስከ አሁን ‹‹የሊኒዬር ኢኮኖሚ ሞዴል›› በመጠቀም ነበር ተረፈ ምርቶችን ሲያስወግዱ የኖሩት። ይህ ሥርዓት ወደ ‹‹ሰርኩላር ኢኮኖሚ ሞዴል›› እየተሸጋገረ ይገኛል። በርካታ ሀገሮችም ይህን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ በማስተዋወቅ ላይ ይገኛሉ።

‹‹ሰርኩላር ኢኮኖሚ ሞዴል›› የሚመራባቸው አልያም የሚያተኩርባቸው ሃሳቦች ተረፈ ምርቶችን እንደገና መጠቀም ወይም የምርት ሕይወት ዑደትን ማራዘም የሚሉት ናቸው። ይህ ሃሳብ ተረፈ ምርቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችሉ መንገዶችን መፍጠር፣ የተረፈ ምርት ውጋጅን መቀነስ የሚያስችሉ ዲዛይኖችን መፍጠር እና ሥራ ላይ ማዋል እና በአመራረት ሂደት ውስጥ የሚኖረውን ተረፈ ምርት ጨርሶ ማስወገድን ይመለከታል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪው ለውጭ ገበያ ከሚቀርቡ ምርቶች እና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬን ከሚያስገኙ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። ዘርፉ በሚያመርትበት ወቅት በአካባቢ በአጠቃላይ በአየር ንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ሲሰራ ቆይቷል። አሁን ደግሞ ዓለም የደረሰበትን የፋብሪካዎች አመራረት እንዲከተል ለማድረግ እየተሠራ ነው።

ከሰሞኑም በአፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያን ጨምሮ አራት ሀገራት ላይ በሙከራ ደረጃ የሚሠራውን የሰርኩላር ኢኮኖሚ በጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ዘርፍ ላይ የማስተዋወቅና የመተግበር ሥራን መሠረት ያደረገ ፕሮጀክት ይፋ ተደርጓል።

ፕሮጀክቱን ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ነው። የሚመራው በዚሁ ተቋም ሲሆን በአፍሪካ የሰርኩላር ሞዴል ኢኮኖሚ ኢኒሼቲቭ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና አስተባባሪ፣ የተባበሩት መንግሥታት ኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO)፣ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ የጥናትና ምርምር ልማት ማዕከል በጋራ ሆነው ይሰሩታል። ፕሮጀክቱ ‹‹የሰርኩላር ኢኮኖሚን በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ዘርፍ በማስተዋወቅ ቀጣይነት ያለው የኬሚካል እና ተረፈ ምርት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት›› ልንለው እንችላለን።

ፕሮጀክቱ ይፋ በተደረገበት እለት የተገኙት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሚልኬሳ ጃጋማ የጨርቃጨርቅ ዘርፍ የሚመረትበት መንገድ በተያያዘ የአየር ንብረት እና አካባቢን በይበልጥ ይበክላል የሚባልለት ዘርፍ ነው። ኢንስቲትዩቱ በስሩ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ የጥናትና ምርምር ልማት ማዕከል ያለው ሲሆን ብክለትን ሊቀንሱ የሚችሉ የአሠራር ሥርዓቶች በተለያየ ጊዜ ተግባራዊ

**ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያ በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን፣ የተሻሻለ ምርት እንዲኖር እና በአየር ንብረት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲቀንስ የሚያደርግ ነው**

ይደረጋሉ። በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾችም ሆኑ ፋብሪካዎች ላይ ያላቸው የብክነት እና ብክለት ላይ ያለው የቁጥጥር ሥርዓት እንደሚደረግ ገልጸዋል። አንዱ ኬሜካሎችን ተጠቅመው ምርቶች በሚያመርቱ እና ኬሚካሎችና ፍሳሾችን በሚያስወግዱ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይደረጋል። በመሆኑም የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ፍሳሽ ቆሻሻ ውጋጅን ጨርሶ ማስቀረት (zero liquid discharge waste management ) መንገድን ይከተላሉ። በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ዘርፍ ላይ የሚደረጉ ምርቶች ከአካባቢ ጋር የተስማሙ አካባቢን የማይበክሉ፣ እንዲሁም አምራቾች ተወዳዳሪ ሆነው ምርቶቻቸውን ለገበያ ማቅረብ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ለመፍጠር፣ በሀገር ውስጥና ውጭ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማቅረብ እንዲችሉ አቅም ለመፍጠር የባለሀብቶችን ጥረት ለማገዝ እንዲችል በመንግሥት እና በልማት አጋሮች የተቀረጸ ፕሮጀክት ነው። በዋናነት የሚያተኩረውም የአካባቢ ደህነት ጋር የተያያዘና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የአመራረት ሂደትን መከተል ነው።

የሰርኩራል ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብ በሁሉም የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ኢንዱስትሪዎች ተግባራዊ ለማድረግ የታለመ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ በሙከራ ደረጃ በ10 ፋብሪካዎች ለአምስት ዓመት ተግባራዊ የሚደረግ ፕሮጀክት ነው። የተለያዩ ሀገሮች ምርቶችን ለመግዛት ሕዝብን በማይበድል፣ አካባቢን በማይበክል መልኩ የተመረቱ መሆናቸውን እንደቅድሚያ መስፈርት አድርገው አስቀምጠውታል። ዘርፉ ኤክስፖርት መር በሆነ የልማት አቅጣጫ ላይ እየተመራ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ መንገድ ምርቶች መመረታቸው ሀገራችን የዓለም አንድ አካል እንደመሆኗ በየትኛውም የዓለም ዳርቻ የመሸጥ በስፋት ኤክስፖርት ለማድረግ የምንችልበትን አንድ አቅም ይፈጥርልናል ሲሉ አብራርተዋል።

የተመረጡት ፋብሪካዎች ካላቸው የሥራ ሂደት አንጻር ከአካባቢ ደህንነት ጋር በጣም የተቆራኘ ኬሚካልን በመጠቀም ውጋጆችን በአግባቡ መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል በጥሩ የሥራ ሁኔታ ያላቸው ናቸው ተብለው በምሁራን ጥናት ቴክኒካል መስፈርት የተመረጠ ነው።

የአፍሪካ ሰርኩላር ኢኮኖሚ ኔትወርክ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና አስተባባሪ ቤዛዊት እሸቱ በመድረኩ ላይ የሰርኩላር ኢኮኖሚን ጠቃሚነት ሃሳብ ባነሱበት ንግግራቸው ጊዜው የውድድር ነው ያሉ ገልጸው፣ ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያ በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የተሻሻለ ምርት እንዲኖር እና የአየር ንብረት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ እንዲቀንስ የሚያደርግ ፕሮጀክት መሆኑን አስታውቀዋል።

አስተባባሪዋ እንዳሉት፤ የጨርቃጨርቅ ምርት ዘርፍ በሀገራችን ከፍተኛ የሥራ እድልን ከሚፈጥር እና የውጭ ምንዛሬ በማምጣት ረገድ ለኢትዮጵያ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ዘርፍ ነው። በመሆኑም የዘርፉ ምርቶች የተለያዩ ሂደቶችን ተከትለው ወጪ ወጥቶባቸው፣ ጊዜን እና ጉልበትን ወስደው መመረታቸው ካልቀረ በካይነትን በመቀነሰ መልኩ ቢመረቱ እንደ ሀገር ሲታሰብ ብክለት በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከፍተኛ የውሃ እና የአየር ብክለት የቀነሱ መሆን ከሀገር አልፎ የሀገራችን ምርቶች በዓለም አቀፍ የገበያ ስፍራ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላል ሲሉ አስተባባሪዋ ጠቁመዋል። ይህ የሆነበትን ምክንያት ሲያብራሩም ‹‹የዓለም ገበያው በአሁን ወቅት እንኳንስ የአየር ብክለትን በሚያስከትል መልኩ የተመረቱ ምርቶችን ማህበራዊ መብቶችን ‘SOCIAL RIGHTS’ ያላማከሉ ከሆኑ የመግዛት እድላቸው አነስተኛ ነው›› ብለዋል። ይህ የሰርኩላር ኢኮኖሚ በዘርፉ ላይ ተግባራዊ መደረግም እነዚህን ችግሮች ቀርፎ በሚመረተው ምርት አማካኝነት ወደ ዓለም ገበያ ቀርቦ የኢትዮጵያ ምርቶች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና የሚያመጡትም የውጭ ምንዛሬ ከፍ እንዲል ያደርገዋል›› ሲሉ አብራርተዋል።

አስተባባሪዋ እንዳብራሩት፤ ዓለም አሁን በደረሰችበት ደረጃ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪው እጅግ ከፍተኛ ዝና እና ስም ያላቸው ትልልቅ አምራች ኩባንያዎች በሚፈልጉት ስታንዳርድ የሚያመርቷቸውን ምርቶች ፣ ባነሰ የሰው ኃይል አልያም ዋጋ ይህንን የሰርኩላር ኢኮኖሚ ወይንም የአየር ብክለትን በሚቀንስ እና በማያስጠይቅ ሥርዓት ውስጥ ለማምረት የሚችሉባቸውን ሀገራትን በእጅጉ ይፈልጋሉ።

ኢትዮጵያም እነዚህን መስፈርቶች ከሌሎች ሀገራት በተለየ፣ ጊዜውንና ዘመኑን የጠበቁ ጥያቄዎች መልሳ እና አሟልታ ከተገኘች ኢንቨስትመንትን የመሳብ እድሏን ታሰፋለች፤ ተመራጭነቷም እየጨመረ ይሄዳል ሲሉ በፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረገውን የሰርኩላር ኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስረድተዋል። እነዚህን ሥርዓቶች /systems/ መገንባት የሚያስችል መንገድ ቢፈጠር፣ አልያም ከሌሎች ኢንቨስተሮች ጋር በመሆን መሥራት እና እነዚህን የብክለት መጠንን የሚቀንሱ አማራጮችን በራሱ ገንብቶ መሥራት የሚችል ባለሀብት መበረታታት እና መደገፍ ይገባዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ይህ የሰርኩላር ኢኮኖሚ ከአካባቢ የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆነ እና የአካባቢ ብክለትን በማያስከትል መልኩ ከማምረት ባሻገር ፋብሪካዎች በሚያመርቷቸው ምርቶች ተጠቅመው የሚያስወግዷቸውን ውጋጆች የመቀነስ መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ሥርዓትና ሁኔታን የሚያበረታታ ነው። ዘርፉ በሀገራችን በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር አምራች ኩባንያዎች በስፋት የሚገቡበት እና የሚሳተፉበት በመሆኑ እንደ ሀገር በኢንዱስትሪ ፓርክ ደረጃ ኢንዱስትሪው የሚስፋፋበትን የልማት አቅጣጫ ይከተላል። ይህም በተናጠል የፍሳሽ ማጣሪያዎችን ከመገንባት ይልቅ የጋራ የሆነ የፍሳሽ ማጣሪያ መገንባትና ማስተዳደር እንዲችሉ ያደርጋል።

የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አበበ ተካ የዚህ የሰርኩላር ኢኮኖሚ በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ዘርፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ናቸው። ከዚህ ቀደም ስንከተል በነበረው መንገድ የሊኒዬር ኢኮኖሚ (take-make-waste economy) ማለትም አንድን የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅመን ምርትን ማምረት እና የመጠቀሚያ ጊዜው ሲያበቃ ወደ አካባቢ መልቀቅ ወይም መጣል ነበር ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሰርኩላር ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብ እና አካሄድ ይህ አሠራር መቀየር አለበት የሚል ነው። ጥቅም ላይ የማይውሉ ተረፈ ምርቶችን መልሶ መጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የፈጠራ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ ለሌላ አገልግሎት ማዋል እና ወደ አካባቢ መጣል የመጨረሻው አማራጭ ማድረግ እና የሚጣለውን ውጋጅ መጠን በእጅጉ መቀነስ ዋናው የሰርኩላር ኢኮኖሚ ሃሳብ ነው።

ሌላኛው ይህን ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግም ሆነ ለማሳካት በአመራረት ሂደት ላይ የሚፈጠረውን የሚወገድ ነገር መቀነስ ነው ሲሉም ይጠቁማሉ። በአንድ የአመራረት ሂደት ውስጥ የሚያልፍን ውጋጅ አካባቢው እና ተፈጥሮ ላይ ጉዳት እንዳይኖረው አድርጎ አክሞ መልቀቅ በራሱ ወጪ የሚጠይቅ ነው ያሉት አስተባባሪው፣ በምርት ሂደት ላይ የውሃ እና የኬሚካል አጠቃቀምን መቀነስ፣ የግብዓት አጠቃቀምን ማስተካከል ይገባል ብለዋል።

ሰርኩላር ኢኮኖሚ በነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ያተኩራል፤ ውጋጅ እና ተረፈ ምርትን ከሥርዓት ላይ ማውጣት ወይም መቀነስን ይጠይቃል። ተቋሙ አድርጎታል በተባለው ጥናት ከጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች 94ሺህ ቶን ተረፈ ምርት ይወጣል። ሌሎች ሀገራት በተለየ መልኩ የፈጠራ አቅምን ተጠቅመው ከዚህ ተረፈ ምርት ሌሎች ምርቶችን ያመርታሉ፤ በሀገራችን ተረፈ ምርቶችን መልሶ የመጠቀም ሁኔታ እምብዛም የተለመደ አይደለም። በሀገራችን በዚህ ዘርፍ የሚገኙ ፋብሪካዎችም ተረፈ ምርትን መቀነስ ላይ ሊያተኩሩ ይገባል። ተረፈ ምርትን በቀነሱ ቁጥር ጥራትን ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውንም እየጨመሩ ይሄዳሉ።

ይህ ፕሮጀክት በሚተገበርባቸው ፋብሪካዎች ችግሩን የሚያሻሽሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት እና ማስተካከል ያስፈልጋል። ይህም በአመራረት ሂደት ላይ የሚመጣውን ተረፈ ምርት መቀነስ እና የሚወጣውን ተረፈ ምርት ደግሞ ለተሻሻለ አገልግሎት መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት፣ ልምድ፣ እውቀት መገንባት እና ማስለመድ ያስፈልጋል። በምርት ሂደት ውስጥ በካይና አደገኛ ኬሚካልን ማውጣት ከተቻለ በቀላሉ መልሶ ለመጠቀም ይቻላል።

ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረገው በአምስት ዋና ዋና ኮምፖነንቶች ተከፋፍሎ ነው። የመጀመሪያው የሕግ ሥርዓት ማውጣት፣ ድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ የእውቀት ሥራ አመራር ሥርዓት መገንባት ነው።

በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ውስጥ የሚወገደውን ተረፈ ምርት መልሶ መላልሶ በማጣራት ለብዙ አገልግሎት መዋል እንደሚቻል የገለጹት አቶ አበበ፣ አሁን ከሚሰጡት አገልግሎት የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ብለዋል። ፋብሪካዎች ይህንን በማድረግ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበትን መንገድ መፍጠር እንደሚገባ ጠቁመዋል፤ ለእዚህም ተረፈ ምርቶችን መለየት የሚችል ቡድን መቋቋም እንደሚገባም ጠቁመዋል። የተለዩ ምርቶችን መልሶ በመጠቀም ሂደት የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ለሚችል አካልም ሆነ የሥራ ፈጣሪ ማሰራጨት እንደሚቻልም ጠቁመዋል ።

## ጎሜ

# የቀዬው ጉምጉምታ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ፈንጂ ወረዳ፤ መልከ ጽራር ቀበሌ፤ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ከእኩሌታ ሆኗል። የእድሩ ጡሩንባ ነፊው ድጋፌ፤ በግራ እጁ ጡሩንባውን፤ በቀኙ ደግሞ ከጭቃው ጋር ተጣልቶ፤ ከወደ ሶሉ ግንጥል ብሎ የቦካውን የአንድ እግር ጫማውን ይዞ መንደር ለመንደር ይዳክራል። እንደወትሮው ቢሆን ኖሮ ገና አንድ ሰዓት ሳይሞላ አጠናቆ ወይ ከቤቱ አሊያም ከእመት ባዩሽ ቤት ያደረ ጠጁን በማንቃረር ላይ በሆነ ነበር። ነገር ግን፤ ትናንትና ማታ እስከ እኩለ ሌሊት ጢንቢራው እስኪዞር ሲጠጣ አምሽቶ፤ ከሄደበት ዓለም ድንገት ሲባንን፤ ንጋት 12 ሰዓት አልፏል።

ከራስጌው ያገኘውን ደራርቦ ሲሮጥ ከወጣ በኋላ፤ ከአዳፋው ኮቱ ስር የለበሰውን ቲሸርት ቢጤ ቢመለከት የሚስቱ አስናቁ ሆኖ አገኘው። “አሄ! ደግሞ ካንቺም አልፎ ልብስሽም ይጫወትብኝ አስናቁ...” በማለት፤ በአፉ እያጉተመተመ እንዳይታይ የጃኬቱን አዝራራ ቆልፎ መገስገሱን ቀጠለ። ከዚህ ሁሉ በኋላ፤ ይሄው አሁን፤ እንደነጋበት ጅብ ሰፈር ለሰፈር ያለከልካል። ከሁሉም ቦታ ሳያዳርስ ከእርሱ ቀድሞ የስብሰባው ሰዓት ተቃርቧል።

የመጨረሻውን ልፈፋ በመንደር አራት በእነ አበጋዝ ደበበ መኖሪያ ቤት አካባቢ በማድረግ ላይ ነበር። ከመወየቡም፤ በጭቃ ከላይ እስከ ታች የተመረገው ግራጫ ካኪ ሱሪው በከፊል ያገለገለ ምድጃ መስሏል። የቁመቱ መርዘም ጠቀመው እንጂ እንደ አያያዙ ቢሆንማ ፊቱም ከመለወስ የሚተርፍ አይመስልም። ከኮፍያው ስር ላቦቱ ቁልቁል ከግንባሩ ይዥጎደጎዳል። ሰውነቱ ዝሎ ጉልበቱ እየተብረከረከ፤ እንደምንም ብሎ የሞት ሞቱን ጡሩንባዋን፤ ከአፉ ላይ እንደ ጡጦ ገጠማት።...ጡ!...ጥጥ...ትንፋሹ ተቆራርጦ ጡሩንባዋም ለገመችበት። “ኤዲያ! ምኑ ያላዝናል፤ ይሄኔ ትምባሆ ቢሆንማ ትንፋሹን ከእግር ጣቱም ቢሆን ይስበው ነበር። በአፍንጫው የሚነፋ ይመስል...” ሲሉ፤ የአበጋዙ ባለቤት ከወደ ማጀታቸው ሆነው ብስጭት እያሉ ይራገማሉ።

ጥሎባቸው ስብሰባ አይወዱም፤ ባለቤታቸው ደግሞ ከስብሰባ ቦታ ጠፍተው አያውቁም። ድጋፌ ትንፋሹን ሳብ አድርጎ፤ ኃይሉን አሰባስቦ በድጋሚ እድሉን ሞከረ፤ “ጡ...ጥ..ጡኡኡ..ጥ!...” ድምጽዋ ቢዘበራረቅም በቂ ነበረችና ከሆዱ የተጠራቀመውን አየር ወደ ውጭ አራግፎ በድምጹ ቀጠለ። “ለመልከ ጽራር ነዋሪዎች በሙሉ፤ በዞናችን ውስጥ በየሁለት ዓመቱ ለሚካሄደው ለሞዴል ቀበሌ የሽልማት ሥነ ሥርዓት፤ ቀበሌያችንም እጩ ሆና የተመረጠች በመሆኑ ለ..ዚ... ለዚ....ህ እንኳን ደስ አላችሁ! በማለት፤ በዚህና በሌሎችም ወሳኝ ጉ...ዳዮች ዙሪያ ከማህበረሰቡ ጋር ውይይት ይካሄዳ...ል! በመሆኑም በዛሬው እለት ከጠዋቱ ሶ..ስት ሰዓት ላይ... በቀበሌው የስብሰባ አዳራሽ እንድትገኙ ተብላችኋ...ል!” ኡ..ፍ! አለ፤ ከትከሻው ላይ ኩንታል እንዳወረደ ሰው።

ሕዝቡ ከቀበሌው የስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ተጠግጥጓል። ከወዲህና ወዲያ በጫጫታና ሹክሹክታ ተጥለቅልቋል። ነገር እየጎነጎነ በሊቀመንበሩ ላይ በማሴር ላይ ነው። በየወሬ ጀማው ጎን ለጎን፤ ለሁለትም ለሦስትም በመሆን አፍ ለአፍ ገጥመው ለተመለከታቸው፤ የቡድን ሥራ የተሰጠው ተማሪ መስለዋል። እነርሱ ግን በሊቀመንበሩ ላይ ሲዶልቱ ነበር። አብዛኛዎቹ ከእማሆይ ልኬ ዙሪያ ተኮልኩለው ምኑን እንደሆን እየመከሩና፤ እማሆይን በርቱልን... ምንም እንዳይፈሩ በሚመስል ሁኔታ ያበረታቷቸዋል።

እማሆይ ልኬ ካሉ ነገር አዋቂ፤ ለእውነት መለስ ቀለስን የማያውቁ ደፋርና ግልጽ ሴት ናቸው። እድሜያቸው ገፍቶ ሰባዎቹን ቢዘልቀም፤ ወኔና ጉልበታቸው ግን ወጣቱንም የሚያሽቀነጥር ነው። በዘውዳዊው ሥርዓት ውስጥ፤ አባታቸው እጅግ የታወቁ ባላምባራስ ነበሩ። እማሆይም ድሮውንም ቢሆን ጠመንጃ አንግበው እንደ ወንዱ ሁሉ ዘራፍ የሚሉና ጀብዱ የሚወዱ ሴት ነበሩ። በአንድ ወቅት እማሆይ መነኑና፤ ከገዳም ገቡ፤ በማለት ጉድ ተብሎ በዚያው ከተረሱ ከአስር ዓመት በኋላ ለእህታቸው ሞት መጥተው በዚያው ቀሩ። እያደር ሲታዩ አዋቂነትና መልካምነታቸው እየጎላ መጣ። ዛሬም ሕዝቡ ከቦ እንደ ቦክሰኛ የሚያራግብላቸው፤ የዶለቱትን ድግስ በድፍረት ለሊቀመንበሩ እንዲያቀርቡላቸው ነው።

በእዚህ መሃል ሊቀመንበሩ፤ ከእጃቸው የማይለየውን ግዙፍ ሳምሶናይት መሳይ አጀንዳቸውን አንጠልጥለው ወደ አዳራሹ ዘው አሉ። በፍጥነት ወደ መድረኩ እያመሩ በጨረፍታ የተመለከቱት ፊት ግን እጅግ አስፈሪ ነበር። ከመቀመጫ እየተነሱ የሚያንቋቸውም መሰላቸው። በቶሎ ከመንበረ ወንበራቸው ላይ ጉብ በማለት፤ መነጽራቸውን ከዓይናቸው ዝቅ በማድረግ፤ በያዟት መሃረብ ዓይንና ግንባራቸውን ጠረግ ጠረግ አደረጉ። ጉሮሯቸውንም ሳል ሳል በማድረግ ያለወትሮው ስብሰባውን ያለምንም የመድረክ አጋፋሪ ጀመሩት። “የተወደዳችሁ የቀበሌያችን ነዋሪዎች፤ በመጀመሪያ በማርፈዴ ይቅርታ እየጠየቅኩኝ፤ አንድ የምስራች ልንገራችሁ...በየሁለት ዓመቱ በዞን ደረጃ ለሚካሄደው የምርጥ ቀበሌ ምርጥ ተሞክሮ ሽልማት፤ ወረዳችንን በመወከል በእጩነት ከሚቀርቡት ሦስት ቀበሌዎች መሃከል አንዱ ለመሆን በቅተናልና እንኳን ደስ አላችሁ!” በማለት፤ ፈገግ እያሉ ዓይኖቻቸውን ከጥግ እስከ ጥግ አሽከረከሩት።

የጠበቁት ጭብጨባ..ፉጨትና..ጩኸት እጅግ ደብዘዝና ቀዝቀዝ ያለ ሆነ። የሁሉም አንድ ላይ ቢደማመር፤ የድጋፌን ያህል እንኳን አይሆንም። “ምነው መርዝ እንደበላች አይጥ ቅስስ አላችሁሳ... ደስ አላላችሁም ማለት ነው?” አሉ ንድድ ያለውን ውስጣቸውን በቃላት ለማለዘብ እየሞከሩ። “እረ በጭራሽ...ነገሩን ቀደም ብሎ፤ ጡሩንባ ነፊው ድጋፌ ስለለፈፈልን፤ የደስታውን ጮቤ እዚያው ከመንደር ስለረገጥን እንጂማ ከዚህ በላይ ሊያስደስተን የሚችል ምን ሊኖር ይችላል...” በማለት፤ አብራር ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ምላሽ ሰጣቸው። “ይሄ ቀዳዳ! እንዲያው አፉም እንደ ጡሩንባው፤ ትንፋሽ ባገኘ ቁጥር ሁሉ ጡርር! ማለት ይወዳል።” አሉና ወደ አንዱ አቅጣጫ ቃኘት ሲያደርጉ፤ እማሆይ ከነበሩበት ጫፍ ወሬውና ሹክሹክታው እስካሁንም አልረገበም። ደርሷል ሰዓቱ በሉ ተዘጋጁ እያሏቸው ይመስላል።

ክቡር ሊቀመንበሩ የነገሩ አዝማሚያ ቀድሞውኑ ተረድተውታል፤ ይሄ ሁሉ ሹክ ሹክታ ስለምን እንደሆነ አላጡትም። የቀበሌው ነዋሪ፤ እጅግ ፈታኝና ተፋጦ የሚያፈጣፍጥ ጥያቄ ሲኖረው፤ ከፊት እማሆይን አሰልፎ እንደሚመጣ ያውቁታል። በወሬ ወሬም፤ የታሙበት አጻያፊ ጉዳይ ደርሷቸዋል። ድንገት ወርወር ያደረጉት የሊቀመንበሩ ዓይን፤ ሄዶ ከእማሆይ ዓይን ጋር ተገጫጨ። ተያዩና “እባብ ለእባብ፤ ካብ ለካብ” ተባብለው፤ ሁለቱም ሳይነጋገሩ ተግባቡ። “ክቡር ሊቀመንበራችን ሆይ፤ እኛ በድህነት እሳት መቀመጫችንን እየተቃጠልን፤ በልማትና መዋጮ ሰበብ ከሌለን ፍራንክ ላይ መቀነታችንን አስፈትተው፤ እርሶ ግን ያለምንም ሀፍረት እፊታችን ተቀምጠው ያሞኙናል። የቀበሌውን በጀት ተመሳጥረው በልተው፤ ከአንድ ትልቅ ከተማ ላይ ቪላ ቤት ገንብተዋል አሉ...እንዲያው በወላዲቷ አምላክ ይገፎታለሁ! ይህን አድርገዋል ወይንስ አላደረጉም?” የሚለው የእማሆይ ድምጽ በአደባባይ ሲያፋጥጣቸው ታያቸውና ነገሩን ቀድመው ለማንሳት አመነቱ።

“ዛሬ ሁሉንም ነገር ገልጬ ከቻልኩ አሳምናቸዋለሁ፤ ካልሆነም ያበጠው ይፈንዳ” በማለት ቀልባቸውን ሰብሰብ አድርገው፤ ለክፉም ለደጉም በቅድሚያ የስብሰባውን አጀንዳ ለመፈጸም ጉዳዩን ወደ መጨረሻ ለመነጋገር ወሰኑ። “የዛሬው ስብሰባችን ያስፈለገውም፤ እስካሁን በነበሩን ነገሮች ታይቶ እጩ ሆንን እንጂ፤ ገና አሸናፊዎች አይደለንም። ስለዚህ ለአሸናፊነቱ በቀሩን ጥቂት ጊዜያት ውስጥ በትጋት የምንከውናቸው ነገሮች በመኖራቸው፤ ምን ምን እንሥራ ለሚሉት ጉዳዮች ተወያይቶ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው...” በማለት ውሃቸውን አንስተው ፉት አሉ። “ከሦስት ሳምንት በኋላ፤ ቀበሌያችን አሸናፊ የምትሆንባቸውን፤ የልማትና የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን ለመገምገም፤ ለዚሁ ጉዳይ የተዋቀሩ የኮሚቴ አባላት ከዞኑ ይመጣሉ። ስለመሆኑም በጉብኝታዊ ግምገማቸው ወቅት ነጥባችንን ከፍ ሊያደርጉልን የሚችሉ ተጨማሪ ሥራዎች ላይ የምንረባረብ ይሆናል። የሚይዟቸው መስፈርቶች ብዙ ቢሆኑም፤ ጥቂቱን ለማንሳት ያህል... የእያንዳንዱ ነዋሪ የጤና አጠባበቅና ጽዳት፤ የአካባቢ ጥበቃ፤ ሕዝባዊ ልማቶች፤ የአርሶ አደሩ የመሬት አስተራረስና ምርታማነት፤ የአርብቶ አደሩ ስኬታማነትና ልዩ ተሞክሮ፤ በሕፃናት ልጆቻችን” የትምህርት ገበታ...እና የመሳሰሉት ናቸው።” አሉና አጠገባቸው ወደነበረው ምክትል ሊቀመንበር ዞር አሉና በጆሮው ሹክ ሲሉት፤ ወዲያው በፍጥነት ተነስቶ ወጣ።

“ቀበሌያችን ብቻም ሳትሆን፤ በየዘርፉ ስኬት ላይ ለደረሱና የትጋት ተምሳሌት ሆነው ለተገኙም በግለሰብ ደረጃ፤ በሞዴልነት ተመርጠው የሚሸለሙና የሞዴልነትን የክብር ኒሻን የሚያጠልቁ ይሆናል። ስለዚህ ሁላችንም በቤትና ጓዳ፤ በጓሮና ማሳችን ጭምር ምን ሠርተን ምን እንዳለን ማሰብ እንጀምራለን። ለዚህ ደግሞ ከነገ ጠዋት ጀምሮ፤ አካባቢና ጎዳናዎቻችንን በጋራ፤ ቤትና ከአጥር ግቢያችን ደግሞ በግላችን ማጽዳትና ማልማት እንጀምራለን። በመጀመሪያም፤ ሁላችንም በየአጥር ግቢያችን ውስጥ ሽንት ቤቶችን እንቆፍራለን። ቀደም ሲል ያለን ሰዎች ደግሞ ከቻልን በቆርቆሮ ካጣንም በሸራ አሳምረን ውብና ጽዱ እናደርገዋለን። በዚህ የጽዳት ዘርፍ ማሸነፍ ከቻልን፤ የተነቃቃይ ሽንት ቤቶችን በምንፈልገው ልክ የሚሰጡን ይሆናል” በማለት ጥቂት ትንፋሽ ሳብ ከማድረጋቸው፤ የጅብ ችኩሉ፤ ቸኮል ለጥያቄ እጁን ወደላይ እንደቀሰተ፤ ፈቃዳቸውንም ሳይጠብቅ ብድግ ብሎ ተነሳ።

“በእውነቱ እጅግ ድንቅና የተቀደሰ ሃሳብ ነው፤ የሠራነውን መጥታችሁ ስሙ ከማለት እንዲህ ምን እንሥራና እንዲህ እንሥራ ስትሉን ደስ ይለናል። ጥያቄዬ ግን፤ ምግቡን በልቶ የጠገበውን ሰው እና ልጋብዝህ ማለት ምን የሚሉት ምጸት ነው...ይሄ ተገጣጣሚ ነው ግጥምጣሚ የምትሉት ሽንት ቤት የሚያስፈልገው እኮ፤ ሽንት ቤት ለሌለው እንጂ፤ ሽንት ቤት ስላለህ ተብሎ ሌላ ሽንት ቤት መመረቅ ምን ይፈይድልናል? በቀን አንዴ እየበላን ሁለት ሽንት ቤት መጠቀም፤ በምድሩ ቀርቶ በሰማዩስ አያስጠይቀንም...” የሚያውቀውን ሁሉ ፈጥኖ በማራገፍ አዋቂ የመሆን አባዜ የተጸናወተው ድጋፌ፤ የቸኮልን ንግግሩን አቋርጦ፤ ሰያፍ ገባለት። “አልሰሜን ባይ ግባ በለው!...ማነህ ቸኮል...ተነቃቃይ ሽንት ቤት ሲባል፤ የሚሰጡን ከነጉድጓዱ አይደለም። በደህና ላሜራ ተበጅቶ እንደ ቤት የሚያገለግል ነው። እዚያ ባለፈው ከሐረር ከተማ ውስጥ እንደተመለከትነው፤ የፈድሉ ኪዮስክ ሱቅ ማለት ነው። ምነው ደግሞ የኋላ ቀስ ብለህ ብትጠይቅና፤ በየዛፉ ስር እየተጸዳዱ ቅጠል ከመበጠስ፤ ቅድሚያ የተባልከውን ጉድጓድ ብትቆፍር...” አለ። “በህግ አምላክ! ይህን ሰው አስቀምጡልኝ...” ቸኮል፤ ንድድ ብሎት አካኪ ዘራፍ ማለት ጀመረ።

ሊቀመንበሩ፤ ቀድሞም እንደ እንቧይ ሊፈርጡ የደረሱትን ጎላ ጎላ ያሉ አይኖቻቸውን፤ ተራ በተራ ከሁለቱም ላይ እያጉረጠረጡ፤ “አወቅሽ አወቅሽ ሲሏት...በሉ! ሥርዓታችሁን ይዛችሁ በክብር ተቀመጡ፤ እዚህ የተሰበሰብነው የናንተን የሀረቁ ቤት እንቶፈንቶና ጭቅጭቅ ለመስማት አይደለም። የጀመራችሁትን ኋላ እዛው ትጨርሱታላችሁ። በመጀመሪያ ግብረ ገብነት ይኑራችሁ፤ ጠያቂም ሆነ መላሽ ለመሆን ፈቃድ አልጠየቃችሁም። አንተ ድጋፌ!፤ ወይ ስልጣኔንም ተረከብና አንደኛህን ከዚሁ ወንበር ላይ ተቀመጥ። እንዲያው ሥጋዬ ሆንክና ልቆርጥህ ተሳነኝ። ወንድሜ፤ ምን ዓይነቱን ቅዠት ተመልክቶ ድጋፌ ሲል ስም አወጣልህ እንጂ፤ ድጋፍስ የሚያስፈልገው ላንተው ነበር...” አዳራሹ ሙሉ በሳቅ አውካካ...ሊቀመንበሩ ግን ትክዝ ብለው የተናገሩት ከልባቸው የልባቸውን ነበር ። “ቸኮል፤ ሥርዓት አልባ ችኮላህ እንጂ ጥያቄህስ ልክ ነበር። የሚሰጡን ቤቱን ከነክዳኑ ነው። አንተ ብቻ ለመቆፈር ተዘጋጅ እንጂ፤ ካሳሰበህ ኋላ ላይ ችግኝም ቢሆን ትተክልበታለህ፤ መቼም ከዚያ በላይ አትቆፍር...” በማለት፤ ከተሰብሳቢው ሃሳብና አስተያየት ተቀብለውና የቀጣዩን የቤት ሥራ አቅጣጫ አስቀምጠው እማሆይን ተመለከቱ።

“እማሆይ” አሉ ሊቀመንበሩ። “አቤት!” በማለት ብድግ አሉ። “ቅድም ሊጠይቁኝ የፈለጉት ነገር ምን ነበር?” እማሆይ ልኬ፤ መች በዚህ ይደነብሩና ጉሮሯቸውን ጠረግ ጠረግ አድርገው፤ ገና “እህ...” ከማለታቸው፤ ይተውትና ቁጭ ይበሉ፤ ነገሩን አውቀዋለሁ” አሉ ሊቀመንበሩ። “ይኼ ጉደኛ ጭራሽ ውስጣችንንም ያሰልለው ኖሯል...” በማለት፤ እማሆይ በውስጣቸው ግርምትም ግራ መጋባትም እየተለኮሰ ቁጭ አሉ። “እኔን ታውቁኛላችሁ፤ ለምን እንዲህ አሰባችሁብኝ ብዬም አልወቅሳችሁም። ነገር ግን ባልዋልኩበት አውሎ ስምና ክብሬን ያጎደፈው፤ እፊታችሁ የቆመው ይህ ሆድ አደር ነውና እሱ ግን ቅጣቱን ይቀበላል!” ይበልጥ ግራ መጋባት ሆነ። ግማሹ በሀፍረት፤ ገሚሱ ጭንቅላቱን በመወዝወዝ፤ አንዳንዱም “ሞኝህን ፈልግ” በሚል፤ የአዳራሹ ድባብ፤ መውጫና መግቢያው የተከረቸመ ዋሻ መሰለ። የቀዬው ጉምጉምታ አሁን ከራስ ጋር ሆነ።

**የጠበቀት ጭብጨባ..ፉጨትና.. ጩኸት እጅግ ደብዘዝና ቀዝቀዝ ያለ ሆነ። የሁሉም አንድ ላይ ቢደማመር፤ የድጋፌን ያህል እንኳን አይሆንም። “ምነው መርዝ እንደበላች አይጥ ቅስስ አላችሁሳ... ደስ አላላችሁም ማለት ነው?” አሉ ንድድ ያለውን ውስጣቸውን በቃላት ለማለዘብ እየሞከሩ**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## በገናው በንዝረቱ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ይሄን ሰሞን ጆሮ፤ ከአንድ ነገር ይዋደዳል። እንዲያውም ከመዋደድም አልፎ፤ በፍቅር ጠብ እርግፍ ሲል ይታያል። በጆሮ የገባ ለልብም አይቀርምና፤ ልባችንም ወደ አንድ ውስጣዊ ስውር ዓለም ሲሰወር ይሰማናል። በታከሲው ውስጥ ሆነን፤ እኛና ስሜታችን አብረን ስንሳፈር ይታወቀናል። ጆሮና ልባችን ተመሳጥረው፤ እያሴሩብን ይሁን ምን፤ ግራ ሊያጋቡንም ይችሉ ይሆናል። ታዲያ፤ ወርደን ከጎዳናው ላይ ስንሄድ፤ እግራችን ብቻውን አልነሳ ያለ እንደሆን፤ በውስጣዊ ኃይል ሲነዱ ከአንዱ ቦታ መድረስም አለ። እልፍ ስንል ደግሞ፤ ከቅዱሳተ ንዋያት መደብር፤ አሊያም ከሕንፃዎቹ በታችና በላይ ካሉት የዕቃ መሸጫ ሱቆች ደርሰን፤ ድንገት ከድምጹ ጋር ያለ ቀጠሮ እንገናኛለን። በደጀ ሰላሙ አልፈን፤ ከሆቴልና ካፍቴሪያው ብንገባ፤ ከዚሁ ዋል.. ከዚሁ እደር ያሰኘናል። ለሥጋችን ስንቅ ፍለጋ ከገባንበት ምግብ ቤት፤ ቁጭ ስንል ይሄው ድምጽ በድጋሚ እያቃጨለ፤ ከሆዳችን ቀድሞ ልባችን ይጮኻል። ምነው? ብንለው፤ "ምንም እንዲሁ ደስ ብሎኝ ነው" ለምን? "እንዴ አትሰማም ይሄን ድምጽ!"... ይገርማል፤ እኔ ምልህ ግን የኔ ልብ፤ ብለን ልንጠራው ስንፈልግ፤ እርሱ ግን የለም። ጭልጥ ብሎ ከአንድ ቦታ ነጉዷል። ... በገና እንዲህ አያደርገውም አትበሉ፤ ያደርገዋል። ጆሮ፤ ይህን የበገናን ማራኪና ጎርናና ድምጽ ሰምቶ፤ ሃይማኖቴ... እኔነቴ አይልም። የንዝረቱ ኃይል፤ ልብን በምስጠት ከማንሳፈፍ አይመለስም። ሙዚቃ የስሜቶች ሁሉ ገመድ እንጂ፤ የአንድ ዓለም ነጸብራቅ ብቻ አይደለምና ባንወድም ልባችን ልጥፍ ማለቱ አይቀርም። በገና ከነንዝረቱ፤ ታሪክና ውልደቱ... እንዲህ እየደረደርን በቃላት እንቀኘው።

"በገና"፤ በጥሬ ትርጓሜው መዝሙር እንደማለት ነው። በግእዙ ደግሞ "እንዚራ" የሚል ስያሜ አለው። በሀገራችን ከጥንት እስከ አሁኗ ሰዓት፤ ያለምንም የቅኝት መንሻፈፍ ደርሶ፤ ዛሬም በመዝሙራዊ ደምግባት፤ በሙዚቃዊ መዓዛ ከጆሮና ልባችን ላይ ይንቆረቆራል። ሥጋችንን አጥቦ መንፈሳችንን ይከሽነዋል። መነሻው መንፈሳዊው ዓለም እንደመሆኑ፤ ወደዚያ ገባ ብሎ መጠየቁም የግድ ነው። እንደሚነግረንም፤ በገናን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረደሩት፤ የዓይነ ስውሩ የ"ላሜህ" ልጅ ልጆች ወይንም የ"ኢዮቤል" ልጆች ናቸው። ቢሆንም ግን፤ "በገና" ስንል በጠራን ቁጥር፤ አዕምሯችን የጠቢቡን አባት፤ ንጉሥ ዳዊትን ያስታውሰናል። በገናን እየደረደረ፤ ከታች በእጁ ይዞ ከላይ፤ ከመንፈሳዊው ዓለም በለስን ወደ ምድር ያረገፈ፤ ምናልባትም እንደእርሱ ያለ የለም። የበገናው ጌታ ነው። በገና በዋናነት የሚታወቀው፤ በቤተክርስቲያን ውስጥና በመንፈሳዊ ዓለም ቢሆንም፤ ለዛሬው የዘመናዊ ሙዚቃ ውልደት መሠረት ነው። ቅዱስ ያሬድ ያደገውም ሆነ የተማረው በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። በእጁ፤ ከበገና በላይ የያዘው የሙዚቃ መሳሪያ አለ ለማለት አይቻልም። ምናልባትም ወንድሞቹ መሰንቆና ከበሮ ካልሆኑ በቀር። ቢሆኑም ግን፤ ከወሰን አልባ ውቅያኖስ ውስጥ ጠልቆ እልፍ ዜማዎችን ለማስገር፤ እንደበገና ያለው የቅኝት ማስገሪያ አይገኝም። ከእያንዳንዱ አሥር አውታሮች ውስጥ የሚወጣው ንዝረት፤ በምንፈልገው የዜማ ምት ውስጥ ለማረፍ አመቺ ነው።

ከድምጾቹ በላይ፤ አሠራሩን ተከትሎ ስለሚታየው መልኩ ምን ይሉ ይሆን? "በገና በገነ" ይሉናል። በገናውን ደረደረ፤ አነዘረ እንደማለት ነው። "በገነ" የምትለዋ ቃል ከውስጧ ለዓይን የማይታይ አደገኛ እሳት አለባት። "በገነ" በሌላኛው ጫፍ ነደደ፤ ተቃጠለ... የመሳሰሉትን፤ የሰውኛን ውስጣዊ ባህሪያት የተላበሱ ትርጓሜዎችን ይሰጠናል። "በገና በገነ" ሲባልም፤ በዘፈቀደ ሳይሆን በገና የሚሠራበት እያንዳንዱ ግብዓት የደረቀ አሊያም የተቃጠለ በመሆኑ ስያሜውን ከዚሁ ወሰደው። በበገናው፤ በእያንዳንዱ ማዕዘናት ያሉት እንጨቶች የደረቁ መሆን አለባቸው። ቆዳውም በደንብ ከደረቀ ቁርበት መሆን አለበት። አሥርቱ ጅማቶች ወይንም አውታሮች የሚሠሩት፤ ደህና አድርጎ ከደረቀ ጅማት ነው። የበገና፤ አጀማመሩም ከውስጣዊ ስሜት ጋር የተቆራኘ ምክንያት አለው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፤ የቅዱሱን መጽሐፍ ታሪክ በመንተራስ፤ በገና የተጀመረው የአዳም አምስተኛ ትውልድ በሆኑት በኢዮቤል/በዮባል ልጆች ነው፤ ይላሉ። የአዳም ልጅ ቃኤል፤ ወንድሙን አቤልን ይገድላል። ፈጣሪም "ሰው የዘራውን ነው የሚያጭደው" ብሏልና ከነአገዳደሉ ሳያስቀርለት፤ ቃኤልም በገዛ ልጁ በላሜህ ተገደለ። በእርሱ ሞት ሀዘናቸው የከፋው ልጆችም፤ በገናን በማበጀት የውስጥ ሀዘናቸውን በበገና እንጉርጉሮ መግለጽ ጀመሩ። ከዚያን ጊዜ ወዲህም፤ በገናን ለእንጉርጉሮ ብቻም ሳይሆን፤ በንስሐ ከአምላካቸው ፊት ለመውደቅ፤ ለልመናና ለምሥጋናም ጭምር ይጠቀሙበት ነበር። ይህ በገና የሚያወጣው ድምጽም የራሱ የሆነ ስያሜ አለው። ቤተ ክርስቲያኗም "ድምፀ ማኀዘኒ ወይንም ቃለ ማኀዘኒ" ትለዋለች። ታሪኩ እንሚነግረንም፤ አጀማመሩ ከዮባል ልጆች ሀዘን የተነሳ ነበር። የሚሰጠውም፤ የሀዘንና የእንጉርጉሮ ድምጽ ነውና ስያሜውን ይመስላል። ድምጹን ባደመጥነው ቁጥር አንጀታችንን እያላወሰ በስሜት ደፍቆ፤ በትካዜ የማጥመቅ ኃይል አለው። እልፍ ስንል እንኳን ድንገት ከጆሯችን ውስጥ ጥልቅ ያለ እንደሆነ፤ ከንዝረቱ የተነሳ፤ በዓይናችን ወደ ውጭ ሳይሆን በልባችን ወደ ውስጥ እንድንመለከት ከማድረግም ወደኋላ አይልም። ከጆሮ ደምስር እየገባ መላ ሰውነታችንን ከስሜታችን ጋር የሚያጠላልፍ አንዳች ስውር ማሰሪያ አለው።

በገና ከሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎች ለየት የሚያደርገው፤ የእርሱ ብቻ የሆኑ ባህሪያት አሉት። በሚሠራበት ጊዜ፤ አገኘሁ ተብሎ ለየት ባለ መልኩ ልሥራው አይባልም። የሚወጣው ድምጽ፤ ሁሌም በየትኛውም ጊዜና ቦታ በምክንያትና በዓላማ የታጀበ ነው። በጽሞና ውስጣዊ መንፈስን ለማደስ እንጂ በዳንስ በዳንኪራ፤ በፉከራም ሆነ በሽለላ ሥጋን በቹ በለው! ለማታለል አይውልም። ሁሌም፤ ወይ ከራሳችን ጋር ወይ ደግሞ ከፈጣሪያችን ጋር ለመገናኘት ነው። የበገና ቁሳዊ አካል፤ ከአቀማመጡ ጀምሮ የያዘው ተምሳሌታዊ ትርጓሜ አለው። በዋናነት አራት ክፍሎችን እንመለከትበታለን። ከታችኛው፤ በቆዳ ከተሠራው አራት ማዕዘን፤ በሁለቱም አቅጣጫ በቅስት መልክ የቆሙትን ወደ ጎን አንድ አጣምሮ የያዘው፤ የላይኛው ክፍል፤ ፈቃደ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን። ከላይኛው ጫፍ በመስቀል ቅርጽ፤ በግራና በቀኝ የቆሙት ደግሞ፤ የሚካኤልና የገብርኤል ተምሳሌት ናቸው። አሠርቱ አውታሮች፤ አሥርቱን የሙሴ ትዕዛዛትን ወይንም ቃለ እግዚአብሔርን የሚወክሉ ናቸው። አውታሮቹ ሲደረደሩ፤ ድምጹ የሚወጣው ከታችኛው በቆዳ ከተሠራው አራት ማዕዘን ውስጥ ሲሆን፤ ተምሳሌትነቱ እጅና አውታር ተዋህደው ድምጹን እንደፈጠሩ ሁሉ፤ ሥጋና መለኮት ተዋህደው ከድንግል ማኅጸን ስለማደራቸው ነጋሪ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፤ በሌላ ተጨማሪ ተምሳሌተ ትርጓሜም ያስቀምጡታል። እላይና ታቹ፤ በሥጋና መንፈስ እንዲሁም ግራና ቀኙን በብሉይና ሐዲስ ኪዳን ይመስሉታል።

እጅ አለኝ አሊያም ተመቸኝ ተብሎ እጅ ወደ በገና አይሰደድም። አደራደሩ ትውፊታዊ ሥርዓት አለው። ምን ጊዜም በገና ለመደርደር ስናስብ፤ ወደ አውታሩ የምንልከው የግራ እጅ ጣቶቻችንን ነው። የግራ እጅ አሊያም ጣቶቻችን ካልጎደሉ በስተቀር ማለት ነው። በሳይንሱ ግራና ቀኝ እጆቻችን ከግራና ቀኝ የአዕምሯችን ክፍሎች ጋር የተዛመዱ ስለመሆናቸው ሳይንሱ ይነግረናል። የግራ እጃችን ወደ ቀኝ የአዕምሮ ክፍል ያደላል። ቀኙ የአእምሮ ክፍል ደግሞ ስሜታዊና ከስሜት ጋር የተሳሰረ ነው። ሙዚቃ፣ ስዕል፣ ዳንስ... በአጠቃላይ ኪነ ጥበባዊና መሰል ስሜታዊ ግብሮች የሚበስሉበት ነው። የማይታየውን ዓለም፤ በፈጠራና በምናብ ማሳየት የሚችልና ተመስጦን የሚሻም ጭምር ነው። ታዲያ ከሳይንሱ በፊት፤ የኛ አባቶች በገናን በግራ እጅና ጣት እንዲደረደር ማለታቸው፤ በመንፈስ ብቻም ሳይሆን፤ በእውቀትና በጥበብም፤ የደረሱብትን አያሳይም ተላላችሁ... በገናውን ስንደረድር በሁለት ዓይነት መንገዶች ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው፤ የእጆቻችንን ጣቶች በመጠቀም እንቀኛለን። ሁለተኛው ደግሞ፤ በድሕንጻ ነው። "ድሕንጻ" በገናውን አውታር ለመግረፍ የምንጠቀምበት አጫዋች ነው። አውታሮቹን፤ በቀጥታ በጣቶቻችን ከመነካካት ይልቅ በድሕንጻ መጠቀሙ፤ የበለጠ ድምጽና መሳጭ ዜማ አንድናገኝ ይረዳናል።



በገናን በቃላት ስለመደርደራችን፤ ሰሞነኛው የአብይ ጾም አልፎም ሳምንተ ህማማት መስታየታችን ነው። ከጾሙ ሳምንታት ሁሉም፤ በህማማት ወቅት በተለየ ሁኔታ የበገና ድምጽ ከወዲያና ወዲህ፤ ..እርር!... ድርር! ድርን!..ድር!.. ሲል እንሰማለን። እራስን ከማግኘት በላይ፤ ፈጣሪን ለማግኘትና ለመገናኘት፤ ፋይዳው በብዛት ይጎላል። "ድምፀ ማኀዘኒ" ወይንም የሀዘን ድምጽ የሚለውን ትርጓሜን፤ ከመቼውም በላይ በትክክል ይገልጽልናል። ምክንያቱም ደግሞ፤ በስቅለቱ ያለውን የሀዘን ድባብ ይፈጥራል። መድረሱንም ጭምር ይነግረናል። ከዚህ በተለየ መነጽር ለመመልከት ከሞከርን፤ አንድ ጥያቄ ልንጠይቅ እንችላለን። በገናና የአብይ ጾም፤ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የሚያገናኛቸው ነገር አለ ወይ? በማለት ሊቃውንቱን ብንጠይቅ፤ ምላሹ "ምንም የለም" የሚል ይሆን ነበር። ነገር ግን፤ በገናና የአብይ ጾም ለመቆራኘታቸው፤ አንድ ታሪካዊ ምክንያት አለ። ይኸውም፤ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነበር። በዚያን ጊዜ ታዲያ፤ በአብይ ጾም ወቅት፤ በሬዲዮ ከሕዝቡ ጆሮ የሚንቆረቆረው ሁሉ የበገና ድምጽ ነው። በገና፤ የሕዝቡን ልብ እንደፈለገ ውሎ ያመሻል። ውስጥን ዳሳሽ ንዝረቱ፤ ሞገዱን እየዳበሰና እያለሰለሰ፤ አልፎ ከስሜት ጋር ተቆራኘና፤ አብይ ጾም በመጣ ቁጥር ሁሉ በገና የሚናፈቅ ትዝታ ሆኖ ቀረ። ጆሮ ስሙ ስሙ፤ ልብም አምጡ አምጡ ማለት ጀመሩና በገናን ከሰሞኑ ለሰሞኑ ያስመሰሉት ቢሆንም፤ እንደ ቤተ ክርስቲያኗና የሊቃውንት አስተምህሮ፤ በገና በ365ቱም ቀናት በእኩል የሚደረደር ነው።

በገናና በታሪክ ቅኝት የኋልዮሽ መለስ ስንል፤ እድሜው ከ5 ሺህ ስምንት መቶ በላይ ሆኖ እናገኘዋለን። አዛውንትም፤ ሽማግሌም ብለን ለመግለጽ ብናስብ፤ ቁጥሩ ከቃላት በላይ ይሆንና "ቃል አጣሁልህ" ያስብለናል። ከሀገራችን ኢትዮጵያ ጋር ትውውቅ የፈጠረበት ጊዜ በውል ባይታወቅም፤ በዓለም የመጀመሪያዋ አሊያም ሁለተኛዋ ደርዳሪ ስለመሆኗ ግን ጥርጥር የለውም። የበገና እናት፤ ኢትዮጵያ ወይንስ እስራኤል? ምላሹ በራሱ፤ ጥያቄ አጫሪ ይሆንና፤ ገላጋይ ዳኛ የሌለበትን ዳገት ያሳየናል። በገና፤ በንጉሥ ዳዊት ቤት፤ ምግብና ውሃ እንደነበር ቅዱሱ መጽሐፍ ይነግረናልና "እውነቱን ተናግሮ በመሸበት ማደር" ሲሉ፤ ውልደቱ በእስራኤል ነው በማለት የሚሞግቱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ጥቂት አይደለም። ወደ ኢትዮጵያ የመጣውም፤ ሁለቱ ሀገራት በፍቅር በወደቁበት፤ በዘመነ ሰለሞን ጊዜ ስለመሆኑ ይናገራሉ። "ኧረ በጭራሽ!"፤ የሰው ዘር መገኛ፤ የሁሉም ነገር መጀመሪያ፤ የቅዱስ ያሬድ ሀገር ኢትዮጵያ እያለችማ ከእስራኤል ነው አንልም በሚል እሳቤ፤ ሽንጣቸውን ገትረው "ኢትዮጵያ!" የሚሉትም እንዲሁ ጎራ ይዘው አሉ።

ነገርዬው፤ ከወዴትም ይሁን ከማን፤ እራሱን በገናን በዜማ አባብሎ ለመጠየቅ የቻለ፤ ምላሹን ከራሱ ያገኘው ይሆናል። በጀመረ ቢሆን ኖሮማ፤ ስንቱን ጀምረን "እንኩ!" ያልን፤ እኛን ምስኪን መጽዋቾቹን ማን ይደርስብን ነበር...ይህን በመሳሰሉ ጥያቄዎች ድንጋይ አዝሎ ጣና ላይ ከመዋኘትና ኤርታሌ ውስጥ እሳ ከመፈለግ... በያዝነው ነገር ምን ሠራንበት ብሎ፤ ውስጥን ማሰሱ የተሻለ ነው። በራሳችን የታሪክ አሰሳ ውስጥ፤ የበገናው እናት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ እሙን ነው። ከያሬዳዊ የሙዚቃ ፈለግ አንስቶ፤ ወደ ውጭ ከቤተክርስቲያኗ አልፎ መውጣቱ ግን አልቀረም። በቀደሙት የነገሥታቱ ዘመን፤ በገና ከሹማምንቱ ቤት ሁሉ የማይጠፋ ውስጠታዊ ኒሻን ነበር። ከሁሉም በተለየ፤ አፄ ቴዎድሮስ ያለ በገና ውሎ ማደር የሚጨንቃቸው ዓይነት ነበሩ። ፈጣሪያቸውን ለማመስገንም ሆነ፤ የጭንቀት ስሜታቸውን ለማርገብ ሲሹ፤ በገናውን ከተሰቀለበት ውርድ! በማድረግ፤ በቀኝ አንቀብቅበው በግራ የሚያጨዋውቱ ስለመሆናቸው ታሪክ ይነግረናል። እንዲያውም፤ በእሳቸው ዘመን የተደረደረ አንድ የበገና ዜማ፤ ዛሬም ድረስ ለማስተማሪያነት ሲያገለግል እንመለከታለን።

በገናና የኛ ትውልድ፤ ተጠፋፍተው ከረዥም ጊዜያት በኋላ የተገናኙ ዘመዳሞች መስለዋል። እግዜር፤ በገናን ትረፍ ሲለው፤ አንዱን የጥበብ ኖህ አስነስቶ ከመጥፋት አዳነው። እንጂማ፤ ከሀይቅ ጫፍ ላይ ቆሞ እንደሚንደረደር ዋናተኛ፤ በገናም ሲያኮበኩብ ነበር። የበገና አባት ለመባል የበቃው፤ ስብሐት አለሙ አጋ፤ ደርሶ በገናን ታደገው። የደበዘዘውን ማንነቱን እያፈካ፤ እልፍ ተማሪና የበገና ነብስ አድን ሠራተኞችን ለመሰብሰብ ቻለ። በውስጡ ያለውን ልዩ የበገና እውቀትና ችሎታ ለደረሰው ሁሉ እያካፈለ፤ በገናን አፍቃሪ ትውልድ ለመሥራት በቃ። ዛሬ ላይ በየሙዚቃ ትምህርት ቤቱ ሁሉ፤ በገናን በፍቅር አቅፎ በስሜት የሚዳስሰው ወጣት ቁጥሩ በገፍ ነው። እያንቆለጳጰሰና እያባበለ፤ ሙዚቃን ከውብ ዜማ ጋር የሚያልብበትም እልፍ ነው። በአንዱ የአዲስ አበባ ጎዳና ላይ፤ በገናን ከነነብሱ ተሸክሞ፤ በኩራት ወዲያና ወዲህ የሚልን ሰው ለማግኘት፤ ብዙ መጠበቅ አያሻንም። እንደ ገበያና ገበያተኛ፤ ትርምስምስ ብሎ ውጥንቅጡ ከወጣው መንገደኛ መሃል፤ ትኩር ብሎ በዓይን ማንጠር ብቻ ነው። ጎምለል ሲል ከነ በገናው... እሷም ከነበገናዋ... ሲያዘግሙ እንመለከታለን። መውደድ ይስጥህ ካሉ አይቀርም፤ የበገናን ይስጥህ ማለት ነው። ከሞት ተርፎ፤ ሕይወት ማብቀልም ጀምሯል። በመጨረሻም፤ ይህችን እቋጥርለት ዘንድ፤ የገዛ ንዝረቱ አነሆለለኝ።

የበገናው ዜማ ከንዝረቱ፤  
ከአጽዋማት ጀንበር በፍልሰቱ፤  
ልቤን ባውታር፤ ቃኘው በቅኝቱ፤  
በጸባኦት በእግዜር ሰማእቱ።  
ስንኩል ሀሳብ፤ ከመንፈስ ተሰቃቅሎ፤  
ከህማማት ማዕልት ተንከባሎ፤  
እንዳይወድቅ ምሽት ተሰናክሎ፤  
ሲደረደር ያቆም አደላድሎ።  
የሀገሬ ቅኝት በበገናው፤  
እንዴት ያምራል፤ ጎበዝ ከነዜማው፤  
አስር አውታር ባንዱ ተሰባጥረው፤  
ማዕዘናቱም ቁርጥ ሀገሬን ነው።  
ከአጽናፍ አጽናፍ ድሮ ዝንተዓለም፤  
ሙዚቃ ለነብስ፤ ተብላ ሳትቀመም፤  
ይህ በገና ያኔም፤ ነበር ሲያዜም፤  
ከምድር ሆኖ ድጓ ለአርያም።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በዓልን ከአረጋውያን ጋር - በመቄዶንያ

**እዮሩስ ተስፋዬ**

‹‹ሰውን ለመርዳት ፤ሰው መሆን በቂ ነው!›› በሚለው መሪ ሃሳብ የሚታወቀው "መቄዶንያ" የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል›› ጧሪና ደጋፊ የሌላቸውን በተለይም ራሳቸውን ችለው መንቀሳቀስ፣ መመገብ እና መጸዳዳት የማይችሉ የአልጋ ቁራኛ የሆኑና የሰው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አረጋውያንን እና የአእምሮ ህሙማንን ከወደቁበት ጎዳና በማንሳት ወደ ማዕከሉ በማምጣት ድጋፍ የሚያደርግ ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

በአሁኑ ወቅት ከ7 ሺ 500 በላይ የሚሆኑ ተረጂዎችን ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ከሚያገኘው ድጋፍ መልሶ እየደገፈ የሚገኘው ማዕከሉ ትናንት በጎዳና ላይ ወድቀው የነበሩ አረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን ዛሬ ላይ ሕይወታቸው ተቀይሮ በጉልበታቸው እና በእውቀታቸው የደገፏቸውን ማእከል እያገለገሉት ይገኛሉ።

የማዕከሉ መሥራች እና ዋና ሥራ አስኪያጅ የክብር ዶክተር ቢኒያም በለጠ እንደሚገልጹት፤ ሁሌም ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኘው ኢትዮ ቴሌኮም ለማዕከሉ ልዩ ትኩረት በመስጠት እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ‹‹ሚያዝያን ለመቄዶንያ›› በሚል መሪ ቃል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር አመቻችቷል። በዚህም የኢትዮ ቴሌኮም የማህበራዊ ትስስር ገፆችን ለሚቀላቀሉ አዳዲስ ተከታዮች፣ ልጥፎችን በማጋራትና ላይክ በማድረግ የሚገኘው ገቢ ለማዕከሉ እርዳታ ይውላል።ሕብረተሰቡም የኢትዮ ቴሌኮምን ገጽ በመቀላቀል ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም የማህበራዊ ትስስር ገፆች ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኢንስታግራም፣ ዩትዩብ፣ ሊንክዲን እና ቴሌብርን በመቀላቀል፤ እያንዳንዱ ሰው ሰብስክራይብ ሲያደርግ አስር ብር አዳዲስ ተከታዮች ሲቀላቀሉ ደግሞ ሠላሳ ብር ለመቄዶንያ ገቢ እንደሚደረግ በመረዳት ቀላል የሚመስል ነገር ግን ትልቅ ትርጉም የሚሰጠውን እርዳታ እንዲያደርጉ መሥራቹ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



**የማዕከሉ መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ የክብር ዶክተር ቢኒያም በለጠ**

ማዕከሉ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን ደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ አድዋ፣ ባህርዳር፣ ሐረር፣ ጋምቤላ፣ ጎሬ፣ መቱ ፣ጅማ፣አምቦ ሀዋሳ እና አርባ ምንጭን ጨምሮ በ25 ከተሞች ውስጥ እየሠራ ይገኛል።በቀጣይም በተለያዩ ከተሞች ተመሳሳይ አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጀ ሲሆን፤ በወሊሶ፣ ሱሉልታ፣ ሰበታ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሆሳዕና እና ሌሎች ከተሞች ላይ ለመሥራት ከወዲሁ እንቅስቃሴ ጀምሯል። አገልግሎቱን ወደ 20ሺህ ከፍ ለማድረግ እየተሠራ ሲሆን፤ እየተሠራ የሚገኘው ባለ 15 ወለል ሕንፃ ግንባታ ላይ ኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ድርጅቱ ላለፉት አስርት ዓመታት ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እያደረገ ያለው ድጋፍ የሚመሰገን ነው።

ማዕከሉ ያለ ምንም የውጭ እርዳታ እና ድጋፍ ለተረጂዎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። በሙያ፣ በጉልበት፣ በሃሳብ፣ በገንዘብ እና በበጎ ፈቃድ ማገልገል ብዙዎችን መርዳት ነው። እንደ ሠርግ፣ ልደት፣ ኒካ እና መሰል ድግሶች ያሉባቸው ዜጎች ማንኛውንም ፕሮግራማቸውን ከአረጋውያን ጋር በመሆን ማሳለፍ ማህበራዊ ኃላፊነትን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ኃላፊነትን መወጣትም ጭምር ነው።

ሥራ አስኪያጁ እንደሚያብራሩት፤ በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ያለው የማዕከሉ ሕንፃ ሆስፒታል እንዲሆን በማሰብ እየተገነባ ነው። ሕንፃውን ገንብቶ ለማጠናቀቅ 1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል። ስለዚህ ሁሉም የቻለውን እና የአቅሙን በማድረግ ጎዳና ላይ የወደቁትን አረጋውያን እንዲሁም የአእምሮ ሕሙማንን ለመርዳት በሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድጋፍ በማድረግ ሊያግዝ ይገባል።

ለመቄዶኒያ እዚህ መድረስ የብዙዎች ድጋፍ አለበት። ከግለሰቦች ጀምሮ የተለያዩ ማህበራት፣የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑት ተቋማትን ጨምሮ ድርሻቸው ከፍተኛ የሚባል ነው። ይህንን ድጋፍ መሠረት በማድረግ ዛሬም ቢሆን ወደ መቄዶኒያ በቀን በትንሹ እስከ አስር ሰው ከጎዳና ተነስቶ ወደ ማዕከሉ ይገባሉ።

‹‹ብዙ ሰዎች መቄዶኒያ አቅም ያለው ይመስለዋል ነገር ግን በጣም ብዙ ወጪ ነው ያለብን።›› የሚሉት ሥራ አስኪያጁ ለምሳሌ በቀን ከ70 በላይ የሚሆኑ የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ታካሚዎች ወደ ህክምና ተቋማት ይወሰዳሉ። ለህክምና ብቻ ብዙ ወጪ ያወጣል።በተመሳሳይ አልጋ ቁራኛ ለሆኑ ታማሚዎች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እና መሰል ነገሮችን ለመግዛት ወጪዎችን ያወጣል። ሌላው የተሽከርካሪ እጥረት ፣ሕንፃውን ገንብቶ ለማጠናቀቅ እና ግብአቶችን ለማሟላት በአጠቃላይ ብዙ የጎደሉ ነገሮች ያሉት መሆኑን ሕብረተሰቡ ተገንዝቦ ያለውን መርዳት ይጠበቅበታል።

ከሁለት ቀናት በኋላ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረውን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ በዓልን በተመለከትም የተለያዩ የምግብ ፍጆታዎች፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን እንዲሁም ለበዓል የሚሆን የእርድ ከብት እና አቅማቸው የፈቀደውን ይዞ በመምጣት በዓሉን ከአረጋውያን ጋር በደስታ እና በምርቃት እንዲያሳልፉ ሥራ አስኪያጁ ጥሪ አቅርበዋል።

# ዓለም አቀፍ



## እንግሊዝ የመጀመሪያዎቹን ፈቃደኛ ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ሩዋንዳ ሳከች

እንግሊዝ የመጀመሪያዎቹን ፈቃደኛ ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ሩዋንዳ ላከች። እንግሊዝ በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተው መርሀ ግብሯ የመጀመሪያዎቹን ጥገኝነት ጠያቂ ስደተኞችን ያለፈው ሰኞ እለት ወደ ሩዋንዳ መላኳን ተዘግቧል።ዘገባው ወደ ሩዋንዳ በረዋል የተባሉት ስደተኞች ማንነት ግልጽ አለመሆኑንም ጠቅሷል።

ይህ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተው ስደተኞችን የማስወጣት መርሀ ግብር እንግሊዝ በሚቀጥሉት ወራት በግዴታ ለማስወጣት ካቀደችው እቅድ የተለየ ነው ተብሏል። እንግሊዝ በፍቃደኝነት ወደ ሩዋንዳ ለመሄድ ፍቃደኛ የማይሆኑትን በግዴታ የምታስወጣው በእንግሊዝ ቻናል በኩል በትንንሽ ጀልባዎች ወደ እንግሊዝ ለመግባት የሚሞክሩ ስደተኞችን ለማስቆም ነው።

የእንግሊዝ መንግሥት በፍቃደኝነት ወደ ሩዋንዳ ለሚመለሱ ስደተኞች ለእያንዳንዳቸው 3ሺ ዶላር እንደሚሰጥ ገልጿል። ስደተኞች እንግሊዝን ለቀው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጣቸው ቢሆንም በዚህ እቅድ ግን ገንዘቡ የሚሰጣቸው በሩዋንዳ ለመኖር ሲስማሙ ነው።

የመንግሥት ቃል አቀባይ እንደገለጹት፤ ከሩዋንዳ መንግሥት ጋር ባላቸው የስደተኞች እና የኢኮኖሚ ትብብር ስምምነት መሰረት ስደተኞችን ወደ ሩዋንዳ መላክ ችለዋል።"ይህ ስምምነት በእንግሊዝ የስደተኝነት ሰነድ የሌላቸው ሰዎች ህይወታቸውን በሰላም ወደሚመሩበት ሰላማዊ ሶስተኛ ሀገር እንዲሸጋገሩ አስችሏል" ብለዋል ቃል አቀባዩ።

ከፈረንጆቹ 2018 ጀምሮ ከጦርነት እና ረሃብ በመሸሽ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች በትናንሽ ጀልባዎች ተጉዘው እንግሊዝ ገብተዋል። መንግሥት ስደተኞችን ከእንግሊዝ 6ሺህ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው ሩዋንዳ ለመላክ ሲነሳ ያጋጠመውን የህግ እና የፖለቲካ ተቃውሞ ለማሸነፍ ሁለት ዓመት ፈጅቶበታል፡ ፡በመጨረሻም ፓርላማው ከፋፋይ የተባለውን እቅድ ባለፈው ሳምንት ማጸደቁን ጠቅሶ አል ዐይን ዘግቧል፡፡

በአነስተኛ ጀልባዎች ተጓጉዘው የእንግሊዝ ቻናልን በማቋረጥ ከዚያ የሚደርሱትን ጥገኝ ነት ጠያቂዎች ወደ ምሥራቅ አፍሪካዊቱ ሀገር ለማዛወር እና በቋሚነትም ኑሯቸውን ከዚያ እንዲያደርጉ በማቀድ ሁለቱ ሀገሮች የተፈራረሙት ስምምነት ሁለት ዓመታት ማስቆጠሩ ይታወሳል።



## የ98 ዓመቷ አዛውንት በተኩስ መሃል 10 ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዘው ከሩሲያ ጦር አመለጡ

የ98 ዓመት እድሜ ያላቸው የዩክሬን አዛውንት ሴት በተኩስ መሀል 10 ኪሎ ሜትር ርቀት በእግር ተጉዘው ከሩሲያ ጦር ማምለጣቸው አነጋጋሪ ሆኗል። አዛውንቷ አሁን በሩሲያ ቁጥጥር ስር ከወደቀችው ኦቸርታዮን ተነስተው የዩክሬን ጦር ወደ ተቆጣጠረው ቦታ መድረስ ችለዋል።

የዩክሬን ፖሊስ ሰኞ እለት በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በለቀቀው ቪዲዮ ሊዲያ ስቴፋኒቫ የተባሉት ሴት ያለምግብ እና ውሃ እየወደቁ እና እየተነሱ መድረሳቸውን ይናገራሉ። "ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተርፌያለሁ፣ ከዚህም እየተረፍኩ ነው" ሲሉ ስቴፋኒቫ ምርኩዝ ተደግፈው አልጋ ላይ ቁጭ ብለው ሲናገሩ ተደምጠዋል።"ምንም የቀረኝ የለም፤ ቀየየን በእግሬ ተጉዤ ለቅቄያለሁ"።

አዛውንቷ ሩሲያ በሀገራቸው ዩክሬን ላይ እያካሄደች ያለው ጦርነት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጋር እንደማይመሳሰል ተናግረዋል።"ቤቶች እየተቃጠሉ ነው፤ ዛፎች እየተነቀሉ ነው"በማለት የአሁኑን ጦርነት አስከፊነት ገልጸዋል።የዩክሬን የሀገር ውስጥ ሚኒስትር በጽረ ገጹ ላይ ባወጣው መግለጫ ሴትዮዋ በዩክሬን ጦር በሌሊት መገኘታቸውን እና ተፈናቃዮቹ ወደሚጠለሉበት ለወሰዳቸው ፖሊስ መስጠታቸውን ገልጿል።

ሚኒስቴሩ "የህግ አስፈጻሚ አካላት የሴትዮዋን ቤተሰቦች እያፈላለጉ ነው" ብሏል። በፈረንጆች የካቲት 2022 የተጀመረው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት አሁንም ቀጥሎ እየተካሄደ ይገኛል ሲል አል ዐይን ዘገባ አመልክቷል።

# የግብርናውን ዘርፍ ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የግብርናውን ዘርፍ ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡

የዲጂታል ግብርናን ለማሳደግ የባለድርሻ አካላት ውይይት ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፍሬው ተገኝ( ዶ/ር) በውይይቱ ወቅት እንዳሉት፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የግብርናው ዘርፍ ዲጂታላይዝ መደረግ አለበት፡፡

የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን ዋናው ዘዴ ዲጂታላይዝ ማድረግ ነው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ዘርፉ ዲጂታላይዝ ሲደረግ አርሶአደሩ በቀላሉ የሚፈልገውን መረጃ ፣የምክር አገልግሎት እንደሚያገኝና የግብዓት ጥያቄውም ይሟላለታል ብለዋል፡፡

በዘርፉ በተለይም በግብዓት አቅርቦት ላይ የተጀመሩ የዲጂታል ሥራዎች እጅግ አበረታች ውጤት እንደታየባቸው የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሥራዎቹ ከባለድርሻ



**ፍሬው ተገኝ( ዶ/ር)**

አካላት ጋር በጋራ በመሆን በስፋት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የዲጂታል ግብርና ከፍተኛ ዳይሬክተር ጪሚዶ አንጫላ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ "ኢ ቮቸር" የግብዓት አቅርቦትን ለማሻሻል ታስቦ የተሠራ ሥራ ነው፡፡ ሥርዓቱ ማዳበሪያ ስርጭት ላይ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ ጥቅም ላይ ውሏል ብለዋል፡፡

በተለይ የገንዘብ መጭበርበር እንዳይፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው፤ኢቮቸር አርሶ አደሩ ተንቀሳቃሽ ስልኩን ተጠቅሞ ማዳበሪያ ግዥ መጠየቅ እንዲችል በማድረግ የማዳበሪያ ግዢ ሂደቱንም ያሳጥረዋል ብለዋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ ዲጂታላይዝ መሆን አርሶአደሩ ቤቱ ሆኖ በተንቀሳቃሽ ስልክ የሚፈልገውን የምክር አገልግሎት እንዲያገኝ ያስችለዋል የሚሉት ከፍተኛ ዳይሬክተሩ፤ በውጤቱም ምርታማነት በመጨመር አርሶአደሩ ውጤታማ እንዲሆን ያስችለዋል ብለዋል፡፡

ኢቮቸር ትልቁ የግብርና ማነቆ የነበረውን የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ይቀርፋል ያሉት ጪሚዶ(ዶ/ር)፤ የኢንተርኔት ግንኙነት በሌለበት አካባቢ አርሶአደሩ ዳታ በማስገባት የኢንተርኔት መሰረተ ልማት ባለበት አካባቢ በመምጣት ሲስተም ውስጥ ማስገባት እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

የሙከራ ትግበራው በአማራ፣ትግራይ፣ሲዳማ እና በኦሮሚያ ክልሎች መጀመሩን ተናግረው፤ የሙከራው ትግበራ እየሰፋ ይሄዳል ብለዋል፡፡

የልማት ሰራተኞች የዲጂታል እውቀት አነስተኛ መሆን ችግር እንደሚያጋጥም ተናግረው፤ በቀጣይ የሠራተኞቹን ክህሎት ማሳደግ ላይ ይሠራል ብለዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የካፒታል ዴቨሎፕመንት ፈንድ የኢትዮጵያ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ኢብራሂም ማማ ፈንዱ የኢቮቸር አገልግሎት ላይ ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የኢቮቸር ሲስተም ይበልጥ እንዲፋጠን እና ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ዓላማው በአርሶአደሩ ደረጃ ምርትን ለማምረት የሚያስችሉ ሂደቶችን እና በምርት ስብሰባ ሂደቶች ላይ ያለውን ችግር ማቃለል እንደሆነ ጠቁመው፤ አርሶ አደሩ በገቢ ደረጃ የሚያገኘውን ጥቅም ለማሳደግ መታቀዱንም አመላክተዋል፡፡

በመድረኩ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት አመራሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡

# የመዲናዋን ሰላም ለማጽናት ሕዝቡ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ።

ቢሮው የመዲናዋን ሰላም ማፅናት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ከተውጣጡ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ትናንት ውይይት አካሂዷል፡፡

የቢሮው ኃላፊ ሊዲያ ግርማ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ሕዝቡን የሰላሙ ባለቤት በማድረግ ከጸጥታ መዋቅሩ ጋር በተከናወኑ ተግባራት በከተማዋ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ተችሏል፡፡ አሁንም በመዲናዋ ሰላምና ጸጥታ ለማጽናት ሕዝቡ እያደረገ ያለውን ያላሰለሰ ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ከሰላምና ጸጥታ ሥራው ጎን ለጎን በከተማዋ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር ሕዝባዊ ውይይት መደረጉን የገለጹት ወይዘሮ ሊዲያ፤ በዚህም ከኅብረተሰቡ ጋር በተሰራው ጠንካራ የክትትልና ጥቆማ ሥራዎች በከተማዋ ያለው የወንጀል ምጣኔ አምስት በመቶ መቀነስ መቻሉን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማን ሰላምና ጸጥታ ለማድፈረስና ሕዝቡን ለማሸበር የሚጥሩ ጽንፈኛ አካላት ቢኖሩም በሕዝቡና በሰላም ሠራዊቱ ጥቆማና ክትትል እንዲሁም በጸጥታ መዋቅሩ ቅንጅት የሽብር ዓላማውን መቀልበስ ተችሏል ብለዋል።

ከሕዝብ ጋር እየተሠራ ባለው ሥራ መዲናዋን ሰላም የሰፈነባትና ለፅንፈኛ ኃይሎች የጥፋት ተልዕኮ የማትመች ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ ይህንን አጠናክሮ ለማስቀጠል አሁንም ዜጎች ከመንግሥት ጎን ሆነው ሰላምን ማፅናት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ሰላምን ለማስፈን ሕዝብን የሰላሙ ባለቤት የማድረግ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን በመግለጽ፤ በከተማዋ የኮሪደር ልማትንና መሰል ፕሮጀክቶች በሰላምና ፀጥታ ችግር ሳይደናቀፉ ለማስቀጠል እየተሠራ ያለው ሰላምን የማስከበር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል።

ኅብረተሰቡ ለከተማዋ ሰላም ዘብ በመቆም፣ደረቅ ወንጀልን በመከላከልና ጥቆማ መስጠት፣ በየአካባቢወረ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በእርቅ ማእድ በመፍታት ለጸጥታ መዋቅሩ አጋዥ ድርሻውን መወጣት እንደሚጠበቅበት ወይዘሮ ሊዲያ ገልጸዋል።

የውይይቱ ተሳታፊ አቶ ኤልያስ አበበ እንደገለጹት፤ እየተከናወኑ ያሉ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማስቀጠል የመዲናይቱን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር በግንባር ቀደምትነት የሚተገብሩ አመራሮችና የሰላም ሠራዊቶች ተፈጥረዋል፡፡ በቀጣይም ይህ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

ሌላኛው የውይይቱ ተሳታፊ አቶ አምሳሉ አራጌ በበኩላቸው፤ የማህበረሰብ ፖሊሶች በአንድ ስፍራ ላይ ረጅም ጊዜ ሲቆዩ ከመላመድ የተነሳ የሥነምግባር ብልሽት እያሳዩ እንደሆነና ወንጀሎችም ሲከሰቱ እያዩ የሚያልፉበት ሁኔታ እንደሚስተዋል በመግለጽ፤ እንደ ደንብ አስከባሪዎች በየስድስት ወሩም ቢሆን የሥራ ቦታቸው ሊቀያየር እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የቢሮው የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድ አፈጻጸም ለኅብረተሰቡ ገለጻ ተደርጎ ውይይት የተደረገበት ሲሆን፤ በቀጣይም በውይይቱ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በቂ ምላሽ ለመስጠት እንደሚሠራበትም ተመላክቷል።

## ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር በየ 15 ቀኑ የሚታተም

# የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

**ኢያሱ መሰለ**

የሰው ልጅ በተሰጠው የማሰብ ጸጋ ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የመጪውን ዘመን ሁኔታ እያነበበ፤ በሕይወቱ ውስጥ ጎጂና ጠቃሚ ነገሮችን እየለየና መፍትሔ እየሰጠ የመኳዝ ኃላፊነት አለበት፡፡ በተለይም በሕይወት ለመኖር ዋስትና የሚሰጡት እንደ ውሃ ፣ እጽዋት ወይም ደን፣ አፈር፣ የአየር ጸባይ የመሳሰሉት ተፈጥሯዊ ጸጋዎች ምሉዕ ሆነው የመቀጠላቸውን ነገር እያረጋገጠ መኳዝ ግድ ይለዋል። እነዚህ ተፈጥሯዊ ጸጋዎች የሰው ልጅን በሕይወት የመኖር ሁኔታ የሚያስተማምኑ የፈጣሪ ስጦታዎች ናቸው፡ ተፈጥሮን በመንከባከብ እና በማከም የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን በመቆጣጠር ዓለምን እና የአየር ንብረቷን ለሰው ልጆች አኗኗር ምቹና ተስማሚ አድርጎ ማቆየት ከሰው ልጆች ይጠበቃል፡፡

ዛፎች ወይም ደኖች በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ በብዙ መንገድ ሊመነዘር የሚችል ነው፡፡ በፍጡራን የእርስ በእርስ መስተጋብር ውስጥ አንዱ ካልኖረ ሌላውም ሊኖር የማይችልበት የህይወት ሕግ አለ፡፡ በዚህ የተፈጥሮ ሕግ ውስጥ እጽዋት ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

ለምሳሌ የእጽዋት ወይም የደኖች መኖር እርጥበት አዘል አየር እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ የእርጥበት አዘል አየር መኖር ደግሞ ደመና እንዲፈጠር ያደርጋል፤ እንግዲህ ምድራችን በልምላሜ የምትፈካውና አረንጓዴ የምትለብስበት አንዱ ምክንያት ደኖች የሚለቅቁት እርጥበት አዘል አየር ወደ ዝናብነት ስለሚቀየር ነው፡፡ በዚህ ሂደት እንስሳትም ይሁኑ የሰው ልጆች ከምድሪቱ ልምላሜ በሚያገኙት በረከት በሕይወት ለመኖር ዋስትና የሚሰጧቸውን ትሩፋት ያገኛሉ ማለት ነው፡፡ ወቅቱን የጠበቀ ዝናብና የተስተካከለ የአየር ጸባይ ሲኖር ምርትና ምርታማነትም ያድጋል፡፡ እጽዋት ለምርታማነታችን ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በዘለለ የተቃጠለ አየር (ካርቦንዳይ ኦክሳይድ) አስወጥተን ንጹህ (አየር ኦክስጅንን) እንድናገኝም የሚያስችሉ ናቸው፡፡

እንግዲህ ለምርታማነት መቀነስ እና ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንዱ የደኖች ወይም





የእጽዋት መመናመን እንደሆነ ከተረዳን፤ የደኖች መመናመን ከሚያሳድረው አካባቢያዊም ይሁን ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ አንጻር የደን ሽፋንን ማሳደግ ከሀገራት የሚጠበቅ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ለሰከንድ እንኳ መረሳት የሌለበት ነው፡፡ ባለንበት ወቅት ዓለም ትልቅ ትኩረት ሰጥቶት እየሠራበት ያለ ጉዳይ መሆኑም ከዚህ አንጻር ነው፡፡

ኢትዮጵያም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አቅጣጫ ሰጪነት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብርን ይፋ አድርጋ ወደ ሥራ ከገባች ከ2011 ዓ.ም እስከ 2015 መጨረሻ እንደ ሀገር ከሃያ ቢሊዮን በላይ የምግብና የዱር ዛፍ ችግኞች ተተክለዋል። በተያዘው በጀት ዓመትም ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

የችግኞች መተከል በምርታማነታችን ላይ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በተለይም የግብርናው ሴክተር ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው፡፡ የክልል ግብርና ቢሮዎችም በጀት በመመደብ፣ ችግኞችን በማፍላትና አርሶ አደሩን በማንቃት የድርሻቸውን በመወጣት ላይ ናቸው፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮም ችግኞችን አፍልቶ ከመትከል አንጻር ቀደም ባሉት መርሀ-ግብሮች በርካታ ስኬቶችን አስመዝግቧል። ያለፉትን ተሞክሮዎች በመቀመርም በዘንድሮው በጀት ዓመት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

እንደ ክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ በ2016 በጀት ዓመት በሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ ሁለተኛ ዓመት ከባለፉት ዓመታት ልምድ በመውሰድ 60 በመቶ ለጥምር ደንና ለፍርፍሬ እንዲሁም 40 በመቶ ለደን ችግኞች ትኩረት በመስጠት የሚከናወን መሆኑ ተገልጿል፡፡ 210 ሚሊዮን የተለያዩና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞች መዘጋጀታቸውም ተጠቅሷል።፡ ከነዚህም 189 ሚሊዮን የሚሆኑ ችግኞች በ42ሺ ሄክታር መሬት ላይ የሚተከሉ እንደሆኑ የክልሉ ሪፖርት ያመላክታል፡፡

በዚህም ለበልግ ተከላ የሚሆን 62 ሚሊዮን የተለያዩ የደን፣ የአግሮ-ፎረስተሪ፣ የፍራፍሬ፣ የቀርከሃ፣ የመኖ እና ሌሎች ዝርያ ችግኞችን በማዘጋጀት 56 ነጥብ 7 ሚሊዮን ችግኞችን በ12ሺ ሄክታር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ እስካሁን ባለው ሂደት፤ የደን 20ሚሊዮን 619ሺ 103 ፣ የጥምር ደን 15ሚሊዮን 958ሺ 472 ፣ የፍራፍሬ 8ሚሊዮን 494ሺ 639 ፣ የመኖ ዕፅዋት 7 ሚሊዮን 860ሺ 990 ፣ ቀርቀሃ 304ሺ 987፣ ለከተማ ውበት 546ሺ 425 እና ሌሎች 5ሚሊዮን 649ሺ 947 በድምሩ 59 ሚሊዮን 434ሺ 563 ችግኞችን ማዘጋጀት እንደተቻለ እና የበልግ ተከላ ቅድመ ዝግጅቱም ተጠናክሮ እየቀጠለ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡ በዚህም የእቅዱን 95 ነጥብ 8 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት የክረምት ወራትም ከ132 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት መደረጉ ተጠቅሷል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ወትሮም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ የተሻለ የደን ሽፋን ካላቸው ክልሎች ተጠቃሽ እንደሆነ ይታወቃል። ክልሉ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብሩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ የደን ሀብት ሽፋኑን የበለጠ ለማሳደግና ነባሩን (ሀገር በቀሉን) የደን ሀብት አስጠብቆ ለመኳዝ አቅም ይፈጥርለታል፡፡ የፍራፍሬ ችግኞችን መትከሉም በአንድ ድንጓይ ሁለት ወፍ ከሚባለውም በላይ ምርቱን ለክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጭ ተደራሽ በማድረግ በምግብ ራስን የመቻል ዋስትናን ለማረጋገጥ በእጅጉ ያግዛል፡፡ የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትም ያረጋግጣል፡፡

# ስፖርት





# ከ17 ዓመት በታች የሴቶች ብሔራዊ ቡድን ዝግጅቱን አጠናክሮ ቀጥሏል

**ብርሃን ፈይሳ**

በዶሚኒካን ሪፐብሊክ አዘጋጅነት በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ የሴቶች ከ17 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ እንደሚካሄድ ይታወቃል። በየሁለት ዓመቱ የሚደረገው ይህ የዓለም ዋንጫ ዘንድሮ ለ8ኛ ጊዜ የሚከናወንም ነው። ከየአህጉራቱ በዚህ መድረክ መሳተፍ የሚችሉ ሀገራትም የማጣሪያ ጨዋታዎችን በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በሚመራው ማጣሪያ ሦስተኛው ዙር ከቀናት በኋላ ይደረጋል። በዚህ ዙር የደርሶ መልስ ጨዋታ ከሚያደርጉት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድንም ከኬንያ አቻው ጋር ይጫወታል።

በዓለም ዋንጫው ከስድስቱ አህጉራት የተወጣጡ 16 ቡድኖች ሲካፈሉ፤ አፍሪካ በሦስት ሀገራት ትወከላለች። ቡድኖቹን ለመለየትም 25 ሀገራት ብሄራዊ ቡድኖቻቸውን ካለፈው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ አንስቶ በማጣሪያው ጨዋታ በማሳተፍ ላይ ይገኛሉ። አራት ዙር ባለው ማጣሪያም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የደቡብ አፍሪካ አቻውን በመርታት ለሦስተኛ ዙር ማለፉ የሚታወስ ነው። አዲስ አበባ እና ፕሪቶሪያ ላይ በነበሩት ጨዋታዎች አጠቃላይ ውጤት 3 ለምንም የሆነ ውጤት ያስመዘገበው የወጣት ቡድኑ ከቀናት በኋላ በሚያደርገው ሦስተኛ ዙር የማጣሪያ ጨዋታ ከኬንያ ጋር ይገናኛል።

የመጀመሪያው ጨዋታ በተያዘለት መርሀ ግብር መሠረት አዲስ አበባ ላይ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም የሚያደርግ ሲሆን፤ ከዚህም የሚሆነውን ዝግጅት



ቡድኑ ወሳኙን የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ከኬንያ ጋር ያደርጋል፤

አስቀድሞ ጀምሯል። በአሰልጣኝ ራውዳ አሊ እየተመራ ከሚያዚያ 11/2016 ዓ.ም አንስቶ በመሰባሰብ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የህክምና ክፍል የጤና ምርመራ ተደርጎለትም ነው ወደ ዝግጅቱ የገባው። የሜዳ ላይ ተግባር ልምምዱንም በአዲስ አበባ እና አበበ ቢቂላ ስታዲየሞች እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስፖርት ማህበር ሜዳ ላይ እያከናወነ ይገኛል። ዝግጅቱን ተከትሎም የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ረውዳ አሊ በ29 ተጫዋቾች የተጀመረው ዝግጅቱ ወደ 23 በመቀነስ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱን ጠቁማለች።

የወዳጅነት ጨዋታን በሚመለከት ሁለት የታቀደው ሁለት ጨዋታ ለማድረግ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የሴት ቡድኖች ወደ ዝግጅት ባለመመለሳቸው እርስ በእርስ ለማድረግ ተገደዋል። ተጋጣሚው የኬንያ ብሄራዊ ቡድን በቅጣት ላይ የቆየ በመሆኑ ያሉበትን ሁኔታ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ ዝግጅቱ በምን መልክ ሊሆን ይገባል የሚለውን አዳጋች ቢያደርገውም ሌሎች አማራጮችን ለመጠቀም እየተሞከረ ነው። ከዚህ በኋላ በሚኖሩት ቀናትም የቡድን ውህደትና ቅንጅት ላይ ያተኮረ ዝግጅት በማድረግ 11ዱን ተጫዋቾች የመለየት ሥራ ይቀጥላል።

ቡድኑን በቅርቡ የተቀላቀሉ ተጫዋቾች ያሉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ከዚህ ቀደም የሚተዋወቁ በመሆናቸው የቡድን ስሜት የመገንባቱን ሂደት ቀላል ያደረገው መሆኑንም አሰልጣኟ ታስረዳለች።

የቡድኑ አባላትም ይህንኑ የአሰልጣኟን ሃሳብ ይጋራሉ። አምበሏ ሂሩት ተስፋዬ በሁለተኛው ዙር ጨዋታ ላይ ያልነበሩ አዳዲስ ተጫዋቾች ቡድኑን ቢቀላቀሉም በአግባቡ ተግባብተው ዝግጅታቸውን እያደረጉ መሆኑን ገልጻለች። ከአሰልጣኞቻቸው የሚሰጧቸውን የልምምድ አቅጣጫ በመከተል በአንድ የቡድን ስሜት ለውጤታማነት እስከ ጨዋታው ያሉትን ቀናትም ዝግጅታቸውን ቀጥለዋል።

አጥቂዋ ማህሌት ምትኩም የቡድኑ አባላት በሞራልና በወኔ ሀገራቸውን ለማገልገል እየተጉ መሆናቸውን ነው የምትጠቁመው። በዚህ ዙር አዳዲስ ተጫዋቾች ቡድኑን የተቀላቀሉ ቢሆንም ዝግጅቱ አስቀድሞ የተጀመረ መሆኑ ለመግባባት አዳጋች አልነበረም። በአሰልጣኞቻቸው በኩል ከሜዳ ልምምድ ባለፈ በሥነ ልቦናም ዝግጅት ማድረጋቸውም ለውጤታማነት በእጅጉ የሚያግዛቸው እንደሆነም አብራርታለች።

በማጣሪያው ምድብ ሁለት ከዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ተደልድሎ የነበረው የኬንያ ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በጨዋታው እንደማይሳተፍ ባሳወቀው ተጋጣሚ ምክንያት በፎርፌ ወደ ሦስተኛ ዙር ማለፍ ችሏል። በአዲስ አበባ እና ናይሮቢ በሚኖሩት የደርሶ መልስ ጨዋታዎች አሸናፊ የሚሆነው ቡድንም በመጨረሻው ዙር ጨዋታ ከጅቡቲና ብሩንዲ አሸናፊ ጋር የሚጫወትም ይሆናል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ለማዕከሉ አገልግሎት የሚውል የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ በሆለታና በመናገሻ ኮሎቦ የወደቀ ፣ የደረቀና የተንጋደዱ የባህርዛፎች የፈረንጅ ፅድ እና የፓቹላ ዛፎች አጫርቶ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

- ❖ የዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና በጨረታ ለመሳተፍ ሀገር ውስጥ ገቢ ድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፡፡
- ❖ በገንዘብ ሚኒስቴር አቅራቢዎች ዝርዝር የሙያ ዘርፍ ተመዝግበው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
- ❖ መጠኑ ከ500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ሲሆኑ ተጫራቾች ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ
- ❖ ተጫራቾች ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት በጨረታው ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ድርጅቶች የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ 500.00 /አምስት መቶ ብር/ በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
- ❖ ተጫራቾች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን ቦንድ ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ/ በባንክ የተመሰከረበት ሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማስያዝ አለባቸው፡፡
- ❖ ተጫራቾች የሚጫረቱበትን የአንድ ሜትር ኪብ ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዓላትና ቅዳሜ እና እሁድን ሳይጨምር እስከ 10ኛው ቀን ድረስ ከመገናኛ ወደ ሲኤምሲ በሚወስደው መንገድ ጉርድ ሾላ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን 100 ሜትር ገባ በማለት ከውሀ ሥራዎች ከፍ በማለት በአ/አ ከተማ መስተዳደር ቅጥር ግቢ ውስጥ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ሕንፃ ቁጥር 06 ቢሮ ቁጥር በተቀመጠ የጨረታ ሳጥን ማስገባት አለባቸው፡፡
- ❖ የጨረታው ማስታወቂያ የሚቆየው ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ በመ/ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ዘግይቶ የሚመጡ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም፡፡
- ❖ ማዕከሉ ስለ ጨረታው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ❖ ስለ ጨረታው የበለጠ ለመረዳት ከተፈለገ በስልክ ቁጥር አቶ ጌታቸው ለገሰ 0913201168 ወይም 0911337749 እና በአቶ ግርማ አድማሱ 0911608008

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል**



## የልዩ ልዩ እቃዎች ሽያጭ
## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 04/2016

ሆራይዘን አዲስ ጎማ ማ/ኃ/የተ/የግ/ማ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል ፡-

1. የብረት በርሚል 2. ያገለገሉ ብላደሮች 3. ልዩ ልዩ ዕቃዎች 4. የፈርነስ ፍሳሽ ፤ ያገለገለ ዘይት 5. የተቆራረጡ ብረታ ብረቶች 6. የተቆረጡ ጎማዎች

በመሆኑም ፍላጎት ያላቸውን ተጫራቾች በሙሉ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ✓ ተጫራቾች ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባቸው፡፡
- ✓ የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ግንቦት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ በሥራ ቀናት የማይመለስ ብር 150/አንድ መቶ ሀምሳ ብር/ በመክፈል ከኩባንያው የምርት ሽያጭ ቢሮ መግዛት እና እቃዎቹን ማየት ይችላሉ፡፡
- ✓ ተጫራቾች መግዛት የሚፈልጓቸውን እቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ የእያንዳንዱን ዋጋ ከተጨማሪ እሴት ታክስ በፊት በግልፅ ሞልተው፤ ሙሉ ስማቸውንና አድራሻቸውን ጽፈው ከፈረሙበት በኋላ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት እለት ጀምሮ እስከ ግንቦት 10 ቀን 2016 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ በሽያጭ ቢሮ ፊት ለፊት ባለው የጥበቃ በር ቁጥር 2 ቢሮ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡
- ✓ የጨረታ ሣጥኑ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡05 ሰዓት ይታሸጋል፡፡ ጨረታው ግንቦት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡20 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል፡፡
- ✓ ድርጅቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- ንብረት አስተዳደር መምሪያ ቢሮ**

**ስልክ ቁጥር 011-442-15-55/234 ወይም 0943880372 መጠየቅ ይቻላል፡፡**

**ሆራይዘን አዲስ ጎማ ማ/ኃ/የተ/የግ/ማ**